# ህዳሴ የእርቅና የአንድነት
# የሽግግር መንግሥት




ልደቱ አያሌው፤ መጋቢት፥ 2012 ዓ.ም.

# “የኢትዮጵያ ህዳሴ የእርቅና የአንድነት የሽግግር መንግሥት” መቋቋም አስፈላጊነት

(ለኢዴፓ ብሔራዊ ምክር ቤትና ለመገናኛ ብዙኀን ለውይይት የቀረበ መነሻ ሐሳብ)[1]

(ልደቱ አያሌው፤ መጋቢት፥ 2012 ዓ.ም.)

## መግቢያ

ከዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትርነት ሥልጣን መምጣት ጋር ተያይዞ በሀገራችን የተከሰተውና ከፍተኛ የሕዝብ ተስፋ ፈጥሮ የነበረው የለውጥ ሒደት ወደ መክሸፍ አቅጣጫ እየሄደ ነው። ለውጡ ሁሉን አቀፍ በሆነ የሽግግር ተቋምና ከፖለቲካ ፓርቲዎች ድርድር በመነጨ ፍኖተ ካርታ መመራት ሲገባው፣ በተጨማሪም ሀገር አቀፍ ብሔራዊ እርቀ ሰላም በማካሄድና መሠረታዊ የፖለቲካ ቅራኔዎቻችንን በተገቢ የሕግና የመዋቅር ማሻሻያዎች መፍታት በሚያስችል አግባብ መካሄድ ሲገባው፣ ከዚህ በተቃራኒ ገዢው ፓርቲ “እኔው አሻግራችኋለሁ” በሚል የተለመደ መታበይ ሒደቱን ብቻውን ሊመራው በመፈለጉ ከፍተኛ ተስፋ የተጣለበት የለውጥ ሒደት በሚያሳዝን ሁኔታ የመክሸፍ አደጋ ገጥሞታል።

ሥልጣን ሲይዝ የሽግግር ሒደቱን በአግባቡ መርቶ ዘላቂ ለውጥ ለማምጣት ቃል የገባው “የለውጥ አመራር” ሕዝብ የሰጠውን አደራ በአግባቡ ከመወጣት ይልቅ ሳይውል ሳያድር ወደ ሥልጣን ሽኩቻ ውስጥ በመግባት ያለፈው የሃያ ሰባት ዓመት ሥርዓት ተቀጽላ እንጂ እውነተኛ የለውጥ ኀይል አለመሆኑን በተግባር አሳይቷል። በዚህም ምክንያት በአሁኑ ወቅት በሀገራችን መለስተኛ ከሚባሉ ጥገናዊ ለውጦች ባለፈ ሀገሪቱ ትርጉም ባለው የተሐድሶ ወይም የሽግግር ሒደት ውስጥ እንዳልሆነች ግልጽ እየሆነ መጥቷል። የለውጥ አመራሩ የወቅቱን ሒደት ወደ በጎ አቅጣጫ ማሸጋገር ይቅርና ሀገሪቱን “ከድጡ ወደ ማጡ”[2] በሚያስብል ደረጃ ወደ ባሰ አደጋ እየመራት ይገኛል።

ይህ የለውጥ ሒደት ወደ ስኬት ሳይሆን ወደ ክሽፈት እየተቃረበ መሆኑ በግልጽ እየታየ ባለበት በአሁኑ ወቅት ከፊታችን ሊካሄድ የታሰበው ሀገራዊ ምርጫ የፖለቲካ ችግሮቻችንን ከመፍታት ይልቅ ወደ ባሰ ሀገራዊ ቀውስ

---

[1] የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢዴፓ) እና አብሮነት ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ አንድነት (አብሮነት) የወቅቱ የሀራችን የፖለቲካ ችግር አስተማማኝና ዘላቂ መፍትሔ ሊያገኝ የሚችለው አንድ ሁሉን አቀፍ የሽግግር መንግሥት በማቋቋም እንደሆነ አቋም ላይ ደርሰዋል። ነገር ግን ይህ አቋም በተብራራ ሰነድ የተደገፈ ስላልሆነ በኢዴፓ በኩል የተብራራ የፓርቲ ሰነድ እንዲኖር የሚያስችል የመነሻ ሐሳብ እንዳቀርብ በተሰጠኝ ኀላፊነት መሠረት ይህንን ሰነድ በረቂቅነት አዘጋጅቼ ለኢዴፓ ብሔራዊ ምክር ቤት ለውይይት አቅርቤዋለሁ። ነገር ግን ሰነዱ በኢዴፓና በአብሮነት ውይይት ተካሂዶበት የድርጅት ሰነድ ከመሆኑ በፊትና ለመንግሥት በጥያቄ መልክ ከመቅረቡ በፊት ይህ ረቂቅ ለመገናኛ ብዙኀንና ለሕዝብ ይፋ ተደርጎ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ግብዓት ቢገኝ ጠቃሚ እንደሚሆን ስለታመነበት በዚህ መልክ ይፋ እንዲሆን ተደርጓል። ፓርቲው በዚህ ረቂቅ ላይ የራሱን ማሻሻያ አድርጎ በአጭር ጊዜ ውስጥ የራሱን ሰነድ ይፋ እስከሚያደርግ ድረስ ይህ ረቂቅ ሰነድ የእኔ የግል አስተሳሰብ ብቻ እንደሆነ ተደርጎ ሊታይ ይገባዋል።

[2] የለውጥ ሒደቱን አጠቃላይ ግምገማ በሚመለከት “ከድጡ ወደ ማጡ!?” በሚል ርእስ በቅርቡ ለሕትመት ከሚበቃው መጽሐፌ ላይ ማንበብ ይቻላል።

ሊያስገባን ይችላል የሚል ከፍተኛ ስጋት በበርካታ ዜጎች ዘንድ ፈጥሯል። በእኛ እምነት፥ ይህ ስጋት ከተጨባጭ ምክንያት የመነጨ ተገቢ ስጋት ነው። ስኬታማ ሽግግር ባላካሄድንበት ሁኔታ ወደ ሀገራዊ ምርጫ ለመግባት መሞከር ወደ ቅድመ 2010 ዓ.ም. ሁኔታ እንድንመለስ፣ ወይም ወደ ባሰ የሀገርን ህልውና የሚፈታተን የፖለቲካ ቀውስ እንድንገባ ከማድረግ ባለፈ ወደ ዘላቂ መዋቅራዊ ዴሞክራሲ ሊያሸጋግረን አይችልም።

የወቅቱ ውስብስብ የፖለቲካ ችግራችን፣ በሕዝብ የተሰጠውን ዳግም ዕድል በአግባቡ መጠቀም ሳይችል በቀረውና አሁን በሥልጣን ላይ በሚገኘው "የለውጥ ኀይልም" ሆነ የከሸፈ ሽግግርን ተከትሎ በሚመጣ የይስሙላ ምርጫ ሊፈታ አይችልም። ከእንግዲህ ችግራችን ሊፈታ የሚችለው በአንድ የሽግግር ሒደት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ሀገራዊ ጉዳዮች በአግባቡ ለመፈጸም የሚችል አንድ ሁሉን አቀፍ የእርቅና የአንድነት የሽግግር መንግሥት በማቋቋም ነው።

ነገር ግን "የሽግግር መንግሥት መቋቋም አለበት" የሚል አቋም ስንይዝ በቅድሚያ ለምን የወቅቱ የሀገራችን የፖለቲካ ችግር በመደበኛ የምርጫ ሒደት ሊፈታ እንደማይችል አሳማኝ ምክንያት ማቅረብ አለብን። ስለሆነም፥ ምን ዓይነት የሽግግር መንግሥት ያስፈልገናል? በማንና እንዴትስ ሊቋቋም ይችላል? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ከመሞከራችን በፊት፣ "ወደ ምርጫ መግባት የለብንም" የምንልበትን ምክንያት በቅድሚያ ዘርዘር አድርገን እንደሚከተለው እናቀርባለን።

## 1. ምርጫ ምን ለመምረጥ?

በመንግሥት በኩል፥ የዘንድሮው ምርጫ በሕግ በተቀመጠው መሠረት በቅርብ ጊዜ እንደሚካሄድ እየተገለጸ ነው። ያውም በዋናው የዝናብና የጭፍና ወቅት፣ ነሐሴ 23 ቀን። እንዲህ የሚሉን ሰዎች የምርጫው ዕለት እስከሚቃረብና የምርጫውን መራዘም በድንገተኛ አዋጅ እስከሚያሳውቁን ድረስ ሆን ብለው እየዋሹን ነው፣ ወይም የሀገሪቷን ነባራዊ ሁኔታ መረዳት በማያስችል የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ገብተዋል ብለን እናምናለን። በእኛ በኩል ቀደም ሲል በተለያዩ መገናኛ ብዙኀን ለመግለጽ እንደሞከርነው፥ አሁን በምንገኝበት ፖለቲካዊ ሁኔታ ሀገራችን ምርጫ ማካሄድ አለባት ብለን አናምንም። ይህንን የምንለው በዋናነት በሚከተሉት አምስት ምክንያቶች ነው።

### 1.1. ከምርጫ በፊት የተሳካ የሽግግር ሒደት ያስፈልገናል

ሀገራዊ ምርጫ ከማካሄዳችን በፊት፥ ሁሉን አቀፍ የእርቅና የአንድነት የሽግግር መንግሥት አቋቁመን፣ ለለውጡ ስኬታማነት አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ጊዜ ወስደን በአግባቡ ማከናወን የማንችል ከሆነና ሽግግሩ ባልተሳካበት ሁኔታ ወደ ምርጫ የምንገባ ከሆነ፥ የለውጥ ሒደቱ በርግጠኝነት ሙሉ በሙሉ ይከሽፋል። ሀገሪቱም ቅድመ 2010 ላይ ወደ ነበረችበት የትርምስ ሁኔታ ትመለሳለች፤ ከከፋም ትፈርሳለች።

የለውጥ ሒደቱ በከፍተኛ የሕዝብ ተስፋ ታጅቦ የተጀመረ ቢሆንም ብዙም ውሎ ሳያድር በብዙ ችግሮችና ስጋቶች የታጨቀ ሆኗል። ሽግግሩ ሁሉን አቀፍ በሆነ የሽግግር ተቋምና የፓርቲዎች የድርድር ውጤት በሆነ ፍኖተ ካርታ መመራት ሲገባው፣ ገዥው ፓርቲ "እኔው አሸጋግራችኋለሁ" በሚል የተሳሳተ አመለካከት አሳታፊ ባልሆነ መንገድ

ብቻውን እየመራው ይገኛል። እርቀ ሰላም፣ ሀገራዊ መግባባት እና የሽግግር ወቅት ፍትሕን ማስፈን በአንድ የሽግግር ወቅት መከናወን የሚገባቸው ቁልፍ ጉዳዮች ቢሆኑም በእነዚህ ጉዳዮች ዙርያ ምንም ዓይነት የሚጨበጥ ሥራ ሳይሠራ ለምርጫ መዘጋጀት ተጀምሯል።

ገዥው ፓርቲና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለሀገሪቱ የፖለቲካ ቀውስ መነሻ በሆኑ መዋቅራዊ ችግሮች ላይ እስካሁን ምንም ዓይነት የተጨበጠ ድርድር አላደረጉም። በዚህም ምክንያት በተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ያሉ ፈርጀ ብዙ ቅራኔዎች እንኳንስ መፍትሔ ሊያገኙ ይቅርና የበለጠ ወደ ባሰና ውስብስብ ወደ ሆነ ደረጃ እየተሸጋገሩ ይገኛሉ። “በጥልቀት ታድሼ አስተማማኝ ለውጥ ለማምጣት ተዘጋጅቻለሁ” በማለት አብዝቶ ሲምልና ሲገዘት የነበረው “የለውጥ አመራርም” ገና ሁለት ዓመት ባልሞላ ጊዜ በከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት መከሰስ ጀምሯል። በእነዚህ ሁሉ ተጨባጭ ምክንያቶች “የለውጥ ሒደቱ” ወደ ክሽፈት ደረጃ እየተቃረበ መሆኑ ግልጽ እየሆነ መጥቷል።

ስለሆነም በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነን የምናካሂደው ምርጫ የለውጥ ሒደቱ የመጨረሻ የክሽፈት ማረጋገጫ ከመሆን አልፎ ወደ ዘላቂና መዋቅራዊ ዴሞክራሲ ሊያሸጋግረን አይችልም። ከእንግዲህ የታይታ ሳይሆን እውነተኛና ስኬታማ ምርጫ እንዲኖረን ከተፈለገ፣ ምርጫው መካሄድ ያለበት ሕዝብን ሊያሳምን በሚችል መጠን ስኬታማ በሆነ የሽግግር ሒደት ውስጥ ማለፋችንን ካረጋገጥን በኋላ ነው። የከሸፈን የሽግግር ሒደት ተከትሎ የሚካሄድ ምርጫ ወደ ባሰ ብጥብጥና ትርምስ የሚያስገባን እንጂ በምንም ዓይነት ወደ ተሻለ ሀገራዊ ሁኔታ ሊያሸጋግረን አይችልም።

## 1.2. ከምርጫ በፊት የአደጋ ስንጥቆቻችንን በአግባቡ መጠገን ያስፈልጋል

ወደ ምርጫ ዘልለን ከመግባታችን በፊት በአግባቡ ልንጠግናቸው የሚገቡን በርካታ ሀገራዊ የአደጋ ስንጥቆች /Fault lines/ አሉብን።

እነዚህ ስንጥቆች አንድና ሁለት ብቻ ሳይሆኑ በርካታና ፈርጀ ብዙ የሆኑ ስንጥቅጥቆች ናቸው። ለምሳሌ፥ በኦሮሞ የፖለቲካ ልሒቃን መካከል፣ በቀድሞው አዴፓና በህወሓት መካከል፣ በብልጽግና ፓርቲና በህወሓት መካከል፣ በብልጽግና ፓርቲና በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል፣ በሻዕቢያና በህወሓት መካከል፣ በአዲስ አበባ ከተማ የይገባኛል ጥያቄ አቅራቢዎች መካከል፣ በፌደራል መንግሥትና የክልል ጥያቄ በሚያቀርቡ የደቡብ ዞኖች መካከል፣ በመንግሥትና እስካሁን ትጥቃቸውን ባልፈቱ የኦሮሞ የፖለቲካ ኀይሎች መካከል፣ በአጠቃላይም በሀገሪቱ ሕገ መንግሥት ደጋፊዎችና ተቃዋሚዎች መካከል፣ ወዘተ... ያሉ ፈርጀ ብዙ የቅራኔ ስንጥቅጥቆች በእርቀ ሰላምና በብሔራዊ መግባባት ሒደት በአግባቡ ሳይጠገኑ ወደ ምርጫ መግባት ወደ ጦርነት አውድማ እንጂ ወደ ዴሞክራሲያዊ የሥልጣን ሽግግር የመግባት አማራጭ ሊሆን አይችልም። በተለይም ከግብጽ ጋር ከፍተኛ ውዝግብና ፍጥጫ ውስጥ በገባንበትና ብዙ የውጭ ኀይሎች በሀገራችን ውስጣዊ ጉዳይ እጃቸውን እያስገቡ በሚገኙበት በአሁኑ ወቅት ወደ ምርጫ ግርግር ውስጥ መግባት ሀገራዊ ህልውናችንን አደጋ ላይ ሊጥለው እንደሚችል ቆም ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል።

## 1.3. ከምርጫ በፊት ጠንካራ ሀገራዊ እርቅና ብሔራዊ መግባባት መፍጠር አለብን

በዚህ "የለውጥ ሒደት" ቁልፍ በሚባሉና ለወቅቱ ሀገራዊ ቀውስ በዳረጉን የፖለቲካ ቅራኔዎቻችን ዙሪያ አንጻራዊ ሀገራዊ መግባባት ለመፍጠር የሚያስችለን ምንም ዓይነት ድርድር አልተካሄደም። በዚህ ሁኔታ ምርጫ ወደ ማካሄድ ውስጥ የምንገባ ከሆነ የምርጫ ሒደቱ በራሱ እነዚህን ቅራኔዎቻችንን የበለጠ ለማባባስ የሚያገለግል መሣሪያ ይሆናል እንጂ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ ለማካሄድም ሆነ የሕዝብ መንግሥት ለማቋቋም አያስችለንም።

የጽንፍና የብሔርተኝነት ፖለቲካ ከፍተኛ ጡዘት ላይ በሚገኝበትና ማኀበራዊ ሚዲያውም ሆነ አብዛኞቹ መደበኛ መገናኛ ብዙኀኖች የእነዚህ ጽንፈኛና ብሔርተኛ ሃይላት ዐላማ ማራመጃ መሣሪያ በሆኑበት በአሁኑ ወቅት ሊካሄድ የሚችል የምርጫ ዘመቻም ሆነ የምርጫ ሒደት፣ ሀገሪቱን ወደ ባሰ ብጥብጥና ትርምስ እንጂ ወደ ሰላማዊ ሁኔታ ሊያሸጋግራት አይችልም። እንኳንስ በዚህ ዓይነት አሳሳቢ ውጥረት ውስጥ የሚገኝ ሀገርና በአፍሪካ ሁኔታ በአንጻራዊነት የተረጋጋ የሚባል ሀገርም ወደ ምርጫ ሒደት ውስጥ ሲገባ ምን ያህል ወደ ፖለቲካዊ ቀውስ የመግባት ዕድሉ ሰፊ እንደሆነ እየታወቀ ትርጉም ያለው እርቀ ሰላምና ብሔራዊ መግባባት ባልተፈጠረበት ሁኔታ ምርጫ ውስጥ ለመግባት መወሰን በእሳት የመጫወት ዓይነት ቅብጠት ነው።

መሠረታዊ ቅራኔዎቻችን በእርቅና በሀገራዊ መግባባት በአግባቡ ባልረገቡበት ወይም ባልታረቁበት ሁኔታ በምርጫው ወቅትም ሆነ በድኅረ ምርጫው ወራትና ዓመታት የተረጋጋ መንግሥትና ሀገር ሊኖረን አይችልም። በአሁኑ ወቅት ምርጫው ተካሂዶ በሆነ ተዐምር ሰላማዊ ሆኖ መጠናቀቅ ቢችል እንኳን፣ ፌደራል መንግሥቱ በአንድ ገዢ ፓርቲ አሸናፊነት የሚያዝበት ዕድል አይኖርም። የፌደራል መንግሥቱን ሥልጣን ለመያዝ ፓርቲዎች የጥምር መንግሥት ለማቋቋም የሚገደዱ ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪም ኦሮሚያን፣ አማራን፣ ሶማሊያን፣ አፋርን፣ ትግራይን፣ የመሳሰሉ ክልሎችና አዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ ፓርቲዎች የመያዛቸው ዕድል ሰፊ ነው። አንዳንዶቹ ክልሎችም በጥምር እንጂ በአንድ ፓርቲ አሸናፊነት መያዝ የማይችሉበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል።

ዛሬ ፌደራል መንግሥቱም ሆነ ክልሎች በአንድ ገዢ ፓርቲ ብቻ በሚተዳደሩበት ወቅት አንጻራዊ ሰላምና መረጋጋር መፍጠር ካልቻልን በምን ተዐምር ፌደራል መንግሥቱና ክልሎች በበርካታ የከረረ ቅራኔ ባላቸው ፓርቲዎች ቁጥጥር ስር ሲወድቁ ሀገሩ ሰላማዊና የተረጋጋ ሊሆን ይችላል? ሀገሪቱስ በታሪኳ አይታው ለማታውቅ ለዚህ ዓይነት የምርጫ ውጤት ብቁ የሚያደርግ የፖለቲካ ባሕል፣ መዋቅርና ሥርዓት አላት ወይ? እነዚህ መሠረታዊ ጥያቄዎች በዋዛ ፈዛዛ ታልፈው እንዲሁ በችኮላ ወደ ምርጫ መግባት ከእብደት ያነሰ ውሳኔ ሊሆን አይችልም። በአጠቃላይ እንደዚህ ዓይነቶቹን የከረሩ ቅራኔዎቻችንን በአግባቡ ሊያለዝብና ሊያቻችል የሚችል ብሔራዊ እርቅና ሀገራዊ መግባባት መፍጠር ከምርጫ በፊት አሳማኝ በሆነ መጠን ልንሠራው የሚገባን ቁልፍ ጉዳይ ነው። ከምርጫ በፊት በቂ ጊዜ ማግኘትና ሁሉን አቀፍ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም የሚያስፈልገንም እነዚህን ሀገራዊ ኀላፊነቶች በብቃት መወጣት የግድ አስፈላጊ ስለሚሆን ነው።

## 1.4. ከምርጫ በፊት በሀገሪቱ ሰላምና የሕግ የበላይነት መስፈን አለበት

በአሁኑ ወቅት በሥልጣን ላይ የሚገኘው መንግሥት በተወሰነ ደረጃ ከአዲስ አበባና ከክልል ከተሞች ውጪ ሕግና ሥርዓትን በብቃት ለማስከበር የሚያስችል ቁጥጥር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍል የለውም። እንዲያውም መንግሥት ራሱ 'በእንዲህ ዓይነት የሽግግር ወቅት የግጭት መከሰት የተለመደ ነው፤ ግጭቱ መቼ እንደሚቆምም ማናችንም አናውቅም' ከማለት በስተቀር መንግሥት በሀገሪቱ ሕግና ሥርዓትን የማስፈን ቀዳሚ ኀላፊነቱን የመወጣት ዝግጁነት እያሳየ አይደለም።

በዚህም ምክንያት በአሁኑ ወቅት በሀገራችን እንኳንስ ለፖለቲካ ሥልጣን የሚያበቃ ሀገራዊ ምርጫ ለማካሄድ ይቅርና ሰላማዊ የዕለት ተዕለት ሕይወትን መኖር የማይቻልበት ሁኔታ ተፈጥሮል። ተማሪዎች በዩንቨርስቲዎቻችን በሰላም መማር አልቻሉም፤ ህፃናትና ሴቶች በሽፍቶችና በሽብርተኛ ኀይሎች አፈና እየተፈጸመባቸው ነው፤ ሰዎች ከቦታ ቦታ በሰላም ተንቀሳቅሰው ነግደውና አልምተው የሚኖሩበት ሁኔታ የለም፤ ዜጎች በብሔር ማንነታቸው ምክንያት ተወልደው ካደጉበት ከመኖሪያ ቀያቸው በገፍ እየተፈናቀሉ ነው፤ በታሪካችን አይተነው በማናውቀው መጠን ቤተክርስቲያንንና መስጂድን የመሰሉ የአምልኮ ቦታዎች በአደባባይ እየተቃጠሉ ነው፤ የስፖርት ውድድሮችን ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ ማካሄድ አስቸጋሪ ሆኗል፤ ሃይማኖታዊ በአላትን በሰላም ለማካሄድ አስቸጋሪ ሁኔታ እየተፈጠረ ይገኛል፤ ዘረፋና ሙስና ከመቸውም ጊዜ በላይ እየተባባሱ መጥተዋል። እንዲያውም አሁን አሁን በመንግሥት ባለሥልጣናት ላይ በጠራራ ፀሓይ ግድያ የመፈጸም የአሸባሪነት ድርጊት ተጀምሯል።

ይህ የሆነው እንዲሁ ያለ በቂ ምክንያት አይደለም። ለሃያ ስምንት ዓመታት በከፍተኛ አፈና ውስጥ የነበረው ሕዝብ 'ነጻ ወጥተሃል' ሲባል በርግጥም ከነበረበት የፍርሃት ቆፈን ከሞላ ጎደል ነጻ ወጥቷል። ነገር ግን አንድ ሕዝብ ከአፈና አገዛዝ ነጻ ወጥቶ ከፍርሃት ሲላቀቅ፣ ሽግግሩ ከአፈና ወደ ሥርዓት አልበኝነት /Anarchisim/ መግባት ሳይሆን ከአፈና ወደ ሕግና ሥርዓት /Law and Order/ ወደ ሰፈነበት ነጻነት መግባት መሆን ነበረበት። የወቅቱ የሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ መገለጫ ግን ሕግና ሥርዓት ሳይሆን ሥርዓት አልበኝነት ሆኗል። ከፍርሃት የተላቀቀ ሕዝብና ሥርዓት አልበኝነት አንድ ላይ በተገኙበት ሁኔታ ወደ ምርጫ መግባት የበለጠ ሀገራዊ ቀውስን እንጂ ሰላምና መረጋጋትን ሊያመጣ አይችልም።

በአጠቃላይ መንግሥት በሀገሪቱ ሰላምንና የሕግ የበላይነትን የማስከበር ኀላፊነቱን በአግባቡ መወጣት ባለመቻሉ ቀላል የማይባሉ የሀገሪቱ አካባቢዎች በወታደራዊ ኮማንድ ፖስት ስር ለመተዳደር ተገደዋል። በተለይም ከክልል በታች ባለው የመንግሥት መዋቅር የሚገኙ የጸጥታና የፍትሕ መዋቅሮች በአግባቡ መሥራት የማይችሉበት ሁኔታ በመፈጠሩ ህዝቡ መልካም አስተዳደር ብቻ ሳይሆን የአገዛዝ ሥርዓት እንዲኖረው ለመመኘት የተገደደበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ከሁሉም በላይ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት፣ መንግሥት ለመባል የሚያስችለው የመጀመሪያ ተግባር ሰላምንና የሕግ የበላይነትን ማስፈን መሆኑን በመዘንጋት በአደባባይና በድፍረት "ሰላም መች እንደሚመጣና ሀገሪቷ መች እንደምትረጋጋ ማናችንም አናውቅም" በሚልበት ሀገር ምርጫ ለማካሄድ ማሰብ ትልቅ ስህተት ነው።

በዓለም አቀፍ የነጻና ፍትሐዊ ምርጫ መመዘኛ መሠረት አንድ ሀገር ምርጫ ለማካሄድ ሲያስብ መራጮችና ተመራጮች የደኅንነት ዋስትና እንዲያገኙ ማድረግ ያለበት መሆኑ የማይታለፍ ቅድመ ሁኔታ እንደሆነ እየታወቀ እንዲሁ በዘፈቀደ ወደ ምርጫ ለመግባት መወሰን ለዜጎችና ለሀገር ደኅንነት ኀላፊነት ከሚሰማው መንግሥት የሚጠበቅ አይደለም። እንዲህ ዓይነቶቹን መሠረታዊ ከሰላምና ከሕግ የበላይነት እጦት ጋር የተያያዙ ችግሮች ሳይፈቱ ወደ ምርጫ ውስጥ ለመግባት መሞከር በርግጥም የሕዝብን ዴሞክራሲያዊ መብትና የሕግ የበላይነትን የማስከበር ምርጫ ሳይሆን ቀውስንና ግጭትን የመምረጥ ምርጫ ነው። በተለይም እንዲህ ዓይነት ውጥንቅጥ ውስጥ ሆነን ወደ ምርጫ ስንገባ ግብጽን የመሰሉ ባላንጣዎቻችን ውስጣዊ ችግሮቻችንን በማባባስና ወደ ሀገራዊ ቀውስ እንድንገባ በማድረግ ረገድ ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ ቆም ብለን ማሰብ አለብን።

## 1.5. ከምርጫ በፊት አስተማማኝ የምርጫ አፈጻጸም ዝግጅት ያስፈልገናል

እኛ ባለን ግንዛቤ፥ መንግሥት፣ ገዢው ፓርቲ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ መራጩ ሕዝብም ሆነ የምርጫ ቦርድ በዚህ አጭር ጊዜ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ ለማካሄድ የሚያበቃ የኀሊናም ሆነ የድርጅት ዝግጅት የላቸውም። ከፓርቲዎች ዝግጅት አንጻር ገዢው የብልጽግና ፓርቲ ሕጋዊ ዕውቅና ያገኘውም ሆነ ስለሚያራምደው አስተሳሰብ ከካድሬዎቹ ጋር መወያየት የጀመረው ገና በቅርቡ ነው። እንኳንስ በቂ የሚባል የምርጫ ዝግጅት ማድረግ ይቅርና፣ በሀገሪቱ የፓርቲዎች ማቋቋሚያ ዐዋጅ መሠረት ጠቅላላ ጉባኤውን አካሂዶ የፓርቲውን አመራሮች እንኳን ገና አልመረጠም። የፖለቲካ ፕሮግራሙንና መተዳደሪያ ደንቡን በዐዲሱ ፓርቲ ጉባኤ ገና አላጸደቀም። የወደፊት አቅጣጫዬ ነው ያለውን የመደመር አስተሳሰብም እንኳንስ ለአባላቱና ለሕዝቡ፣ ለፓርቲ አመራሮቹም ገና በውል አላስጨበጠም።

አብዛኞቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም እንኳንስ በብቃት ለምርጫ ለመወዳደር ገና ሕጋዊ ዕውቅና ለማግኘት የዐሥር ሺህ ደጋፊዎች ፊርማ በማሰባሰብ ሒደት ላይ ናቸው። እንኳንስ የምረጡኝ ዘመቻ ለማካሄድ፣ ወደ ክልል ከተሞች ሄደው የአዳራሽ ሕዝባዊ ስብሰባዎች ለማካሄድ የሚችሉበት ሰላማዊ ሁኔታ ባለመኖሩ እንደ ልብ መንቀሳቀስ ለመቻል መንግሥት በሀገሪቱ ሕግና ሥርዓት እንዲያሰፍን አጥብቀው በመጠየቅ ላይ ናቸው። አብዛኞቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የለውጥ ሒደቱ ተሳክቷል ብለው ስለማያምኑም በብዙ መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ከመንግሥት ጋር ለመደራደር ገና ጥያቄ በማቅረብ ላይ ናቸው። በአሁኑ ወቅት ከ90% በላይ የሆኑት ፓርቲዎች ምርጫው እንዲራዘም፣ በቁጥር ቀላል የማይባሉት ፓርቲዎች ደግሞ ሁሉን አቀፍ የእርቅና የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም እየጠየቁ ናቸው።

መራጩ ሕዝብ፥ እንኳንስ በነጻ ኀሊና በፓርቲዎች መካከል ያለውን ልዩነት በአግባቡ መዝኖ ድምፅ ለመስጠት ይቅርና፣ ከቦታ ቦታ በነጻነት መንቀሳቀስ የማይችልበት የህልውና ፈተና ውስጥ ነው። ሕዝቡ በአሁኑ ወቅት የሚገኝበት ሥነ ልቦና፥ በነጻና ፍትሐዊ ምርጫ አማካኝነት የራሴ የሚለውን መንግሥት ለማቋቋም የሚያስችለው ሳይሆን፣ በጾም በጸሎት በሀገሩ ላይ ሰላም እንዲሰፍን በየዕለቱ ፈጣሪውን በሚማጸንበት ሁኔታ ላይ ነው የሚገኘው። ሕዝቡ ከፍተኛ የህልውና ስጋት ውስጥ በመግባቱም ምክንያት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና ኢኮኖሚያዊ ብልጽግና ሳይሆን በሚያሳዝን ሁኔታ የአገዛዝ ሥርዓት የሚመኝበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

ምርጫውን በብቃት ማስፈጸም የሚጠበቅበት የምርጫ ቦርድም፥ ምርጫውን በምርጫ ጣቢያ ደረጃ ማስፈጸም የሚገባቸው ከሁለት መቶ ሃምሳ ሺ በላይ የሆኑ ዐዲስ የምርጫ አስፈጻሚዎችንና ከመቶ ሃምሳ ሺ ያላነሱ የምርጫ ታዛቢዎችን መመልመልና ማሰልጠን ገና አልጀመረም። ስለ ምርጫው አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ ሕግጋትንም ገና አውጥቶ አልጨረሰም። በሕግጋቱ ዙሪያ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ማድረግ የሚገባውን ውይይትም ገና በውል አልጀመረም።

በአጠቃላይ፥ ሀገራችን ከሥልጣን ጥያቄ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌለው የሕዝብ ቆጠራ ማካሄድ ባልቻለችበት በዚህ ወቅት ለፖለቲካ ሥልጣን የሚያበቃ ምርጫ በሰላም ልታካሂድ ትችላለች ብሎ ማሰብ በሀገር ህልውና ላይ መቀናጣት ነው።

## 1.6. ምርጫ ማካሄድ ያለብን ሕግ ለማክበር ነውን?

ምርጫው በሕግ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ የግድ መካሄድ አለበት ወይም መራዘም የለበትም ብለው የሚከራከሩ ወገኖች እንደ ዋና መከራከሪያ የሚያቀርቡት ብቸኛ ነጥብ "ምርጫው በሕግ በተቀመጠው ቀን ካልተካሄደ ኪዚያ በኋላ የሚኖረው መንግሥት ሕጋዊነት አይኖረውም፣ ሕገ መንግሥቱም ይጣሳል" የሚል ነው። ነገር ግን ይህ መከራከሪያ ነጥብ በሚከተሉት ሁለት ምክንያቶች ውሃ አይቋጥርም።

በመጀመሪያ፥ እንዲህ ብለው የሚያስቡ ሰዎች ከአሁን በፊት ወይም በአሁን ወቅት ያለውን መንግሥት በሕዝብ የተመረጠ ሕጋዊ መንግሥት ነው ብለው የሚያስቡና ከሃያ ሰባት ዓመቱ የፖለቲካ ቅዠት ያልተላቀቁ ናቸው። እንደዚህ ብሎ የሚያስብ ሰው ሕዝቡ ለምን ያንን ሁሉ መሥዋዕትነት በመክፈል ለለውጥ ሲታገል እንደነበርና አሁን የምንገኝበት ወቅትም ለምን "የለውጥ ሒደት" እንደሚባል የገባው አይመስልም። በሕዝብ የተመረጠ ሕጋዊ መንግሥት ቢኖረን ኖሮ፥ ሕዝቡ በምርጫ የመረጠውን የራሱን መንግሥት በሒደት ከጠላው ጊዜውን ጠብቆ በምርጫ ሊያወርደው ይገባል እንጂ ራሱ የመረጠውን መንግሥት ምርጫ በተካሄደ ማግሥት በዐመፅ ከሥልጣን ለማውረድ ይህንን ያህል ዋጋ የሚከፍልበት ምንም ዓይነት ምክንያት አልነበረም። ቁም ነገሩ የሕገ መንግሥቱ መከበር ጉዳይ ቢሆን ኖሮ ሕዝቡ በመንግሥት ላይ ማመጽም ሆነ በዐመፅ መንግሥትን ለመጣል መሞከሩ የሀገር ክህደት ወንጀል በመሆኑ የተቀመጠውን ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ጥሶ የወቅቱን ለውጥ ለማምጣት ባልቻለ ነበር።

ይህ ለውጥ የመጣው ሕገ መንግሥቱ ተጥሶ እንደሆነ መረሳት የለበትም። ይህም የሆነው ሕገ ወጥ የሆነ ሕዝብ ስላለን ሳይሆን የነበረን ሕግ የአምባገነኖች መሣሪያ ሆኖ እያገለገለ የሚገኝና መጣስ የሚገባው ሕግ ስለነበረ ነው። አሁንም "ምርጫው ቢራዘም ሕገ መንግሥቱ ይጣሳል" እየተባለ የሚቀርበው ክርክር ውሃ የሚቋጥር አይደለም። ትናንት ሕዝቡ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሕገ መንግሥቱን ጥሶ በመንግሥት ላይ እንዳመፀውና ይህንን ለውጥ እንዳመጣው ሁሉ፣ ዛሬም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ሕገ መንግሥቱን ማሻሻልም ሆነ መቀየር ፈጽሞ የማይቻል ነገር እንደሆነ አድርጎ ማቅረብ ስህተት ነው። ለወቅቱ የፖለቲካ ቀውስ የዳረገን ሕገ መንግሥት የውቅቱን ቀውስ ለመፍታት ስንፈልግ እንቅፋት ሆኖ ሊቀጥል አይችልም። ከጅምሩም አንድ ሕግ እንዲወጣና እንዲያገለግል

የሚደረገው የሀገርና የሕዝብን ደኅንነትና ጥቅም ለማስጠበቅ ነው እንጂ እሱ እንዳይጣስ ተብሎ ሀገርና ሕዝብን ወደ ብጥብጥ ማስገባት ከአጠቃላይ የሕግ ዐላማና መንፈስ ጋር የሚፃረር አስተሳሰብ ነው።

ሁለተኛ፥ እየተባለ ያለው 'በሀገሪቱ ሕጋዊ የሚባል መንግሥት እንዲኖር፥ ነጻና ፍትሐዊ ባይሆንም የግድ ምርጫውን ማካሄድ አለብን' ከሆነ፣ ይህም ብዙም ፋይዳ ያለው መከራከሪያ አይመስልም። ምርጫው ሰላማዊ፣ ነጻና ፍትሐዊ እንደማይሆን ልባችን እያወቀ እንዲሁ ሕግ አክብረናል ለማለት ወይም ምዕራባውያኑን ለማስደሰት ብለን የምናካሂደው የታይታ ምርጫ ገንዘብና ጊዜን ከማባከን፣ ከዚያም በላይ ሀገሪቱን ወደ ባሰ ብጥብጥ ከማስገባት ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም። ጽንፈኝነትና ብሔርተኝነት በገነገነበት ሀገር የሚካሄድ ምርጫ ራሱ ጥሩ የጥላቻና የግጭት ማካሄጃ መድረክ ከመሆን አልፎ የሙብት ማስከበሪያ ሒደት ሊሆን አይችልም። በዚህ ዓይነቱ ሒደት መጨረሻ ላይ ሊገኝ የሚችለው ውጤትም የፖለቲካ ቀውስን የበለጠ ከማባባስና ከማወሳሰብ አልፎ ሀገርን ወደ መዋቅራዊ ዴሞክራሲ ሊያሸጋግር አይችልም።

ከሁሉም በላይ እየመረረንም ቢሆን ልንጋተው የሚገባን አንድ እውነታ፥ በአሁኑ ወቅት በሥልጣን ላይ የሚገኘው ፓርቲ በአንድ በኩል የሐሳብ የበላይነት ኖሮት በትክክለኛ ምርጫ ለማሸነፍ የሚችል፣ ወይም በሰላማዊ መንገድ ምርጫ ተወዳድሮ ቢሸነፍ ሥልጣኑን በጸጋ ለመልቀቅ ፍላጎት ያለው ፓርቲ አይደለም። ይህንንም ለማለት የሚያስደፍሩ ምልክቶች በበቂ ሁኔታ በአሁኑ ወቅት እየታዩ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ችግሩን የበለጠ አሳሳቢ የሚያደርገው፣ ይህ ገዥ ፓርቲ ላለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት በሀገራችን በሥልጣን ላይ እንደነበረው ህወሓት መራሹ ኢሕአዴግ ምርጫን አጭበርብሮ በሥልጣን ላይ ለመቀጠል የሚያስችል አቅምና ዝግጅት የሌለው መሆኑ ነው።

አፈና ሲፈጽምብን የኖረው በሚሊዮን የሚቆጠረው የኢሕአዴግ ካድሬ፥ ላለፉት 19 ወራት ከዋናው አመራር ተነጥሎ የለውጥ ሒደቱ ባይተዋር እንዲሆን ተደርጎ ቆይቶል። ከቀድሞው የድርጅቱ አሰራር በተለየ ድርጅቱ ስለሚወስናቸው ውሳኔዎችና ስሚያራምዳቸው አቋሞች እንደ ሌሎቻችን በርቀት በሬድዮና በቴሌቭዥን ሲያዳምጥ ነው የከረመው። ከሁሉም በላይ በታችኛው መዋቅር የሚገኘው ካድሬ የስርዓቱ ተቃዋሚ በሆኑ ወጣቶች በንቀት ሲተች፣ ሲወቅስና ሲሰደብ ነው የከረመው። ይህ በመሆኑም ካድሬው የወቅቱን የለውጥ ሒደት ለመቃወምም ሆነ ለመደገፍ የማይችልበት አጣብቂኝ ውስጥ ገብቷል። ሌላው ቀርቶ በድርጅቱ በኢሕአዴግ መፍረስና በብልጽግና ፓርቲ መመሥረት ዙሪያ በአግባቡ ምክሩንና አስተያየቱን አልተጠየቀም።

በዚህም ምክንያት ይህ በሚሊዮኖች የሚቆጠር የኢሕአዴግ የካድሬ ሠራዊት በአሁኑ ወቅት የብልጽግና ፓርቲ የአፈና መዋቅር ሆኖ ለማገልገል የሥነ ልቦናም ሆነ የመዋቅር ዝግጅት አለው ማለት አይቻልም። ቀድሞ የነበረው የኢሕአዴግ ማዕከላዊ የእዝ ሰንሰለትም ዛሬ እንዳለ የሚቆጠርበት ሁኔታ ላይ አይደለም። በምርጫ አስፈጻሚነት ስምም የገዥውን ፓርቲ ካድሬዎች በምርጫ ቦርድ መዋቅር እንደ በፊቱ እንደ ልብ መሰግሰግ የሚቻልበት ዕድል አይኖርም። በአጠቃላይ ምርጫውን እንደ ድሮው የሞት የሽረት ጥያቄ አድርጎ የመሟሟት ፍላጎት በካድሬው ውስጥ በአሁኑ ጊዜ አለ ማለት አይቻልም። ከሁሉም በላይ ግን ቄሮና ፋኖን የመሳሰሉት ተጋፋጭ ኀይሎች እንዲህ በቀላሉ እንደ ቀድሞው ሁኔታ ለካድሬዎች ማጭበርበርና አፈና እጃቸውን የሚሰጡ አይሆኑም። እንዲያውም በአሁኑ ወቅት

ከብልጽግና ፓርቲ ካድሬዎች በላይ የተሻለ የአሸናፊነት ሥነ ልቦና ይዘው የሚገኙት እነዚህ ከመንግሥት መዋቅር ውጭ ያሉ የወጣት አደረጃጀቶች ናቸው።

ስለሆነም እንዲህ ዓይነት አቅጣጫ የጠፋበትና በሐቅም ሆነ በማጭበርበር ምርጫን ለማሸነፍም ሆነ ለመሸነፍ ዝግጁ ያልሆነ፣ ነገር ግን በማንኛውም መንገድ በሥልጣን ላይ መቀጠል አለብኝ ብሎ የወሰነ ፓርቲ በሥልጣን ላይ በሚገኝበት ሁኔታ ወደ ምርጫ መግባት ሀገራዊ ቀውስን የመምረጥ እንጂ ሕጋዊ መንግሥትን ለመምረጥ የሚያበቃ ምርጫ አይሆንም። ስለዚህ የተጀመረውን የለውጥ ሒደት ከክሽፈት አደጋ አውጥቶ ወደ ስኬት ለማሸጋገር እንዲቻል ከተፈለገ በአስቸኳይ ሁሉን አቀፍ የእርቅና የአንድነት የሽግግር መንግሥት አቋቁመን ምርጫውን ሁለት ዓመታት ለሚሆን ጊዜ ማራዘም አስፈላጊ ነው።

ከዚህ ውጭ፥ የምንፈልገውን ውጤት እንደሚያስገኝልን ርግጠኛ ወዳልሆንበት ምርጫ ተጣድፈን መግባት፥ ዕድለኛ ሆነን በሆነ ተዐምር ወደ ባሰ ትርምስ ሳያስገባን ቢቀር እንኳን የሚያስገኘው ዐዲስ ፋይዳ አይኖርም። ደግሞስ ለሺ ዘመናት በአምባገነን ሥርዓት ሲገዛ የኖረ ሕዝብና ሀገር ለበጎ ውጤት ሲባል በስምምነት በተቋቋመ የሽግግር መንግሥት ለሌላ ሁለት ዓመታት ቢተዳደር ምን ተዐምር ይፈጠራል? እንኳንስ በስምምነትና በድርድር በሚቋቋም የሽግግር መንግሥት በተጭበረበረ የምርጫ ሒደት በተመረጠ አምባገነናዊ ሥርዓት መገዛትስ ለኢትዮጵያዊያን ያልለመድነው ዐዲስ ነገር ሆኖ ነው የምርጫውን መራዘም ይህንን ያህል የሞት የሽረት ጉዳይ አድርገን የምናየው?

ምርጫ ካልተካሄደ በስተቀር የሕጋዊነት ቀውስ እንደሚፈጠር ተደርጎ በህወሓትና በአንዳንድ ግልብ እይታ ባላቸው ፖለቲከኞች የሚቀርበው ክርክር የሀገራችንን ነባራዊ ሁኔታ በአግባቡ ያገናዘበ አይደለም። ኢትዮጵያውያን በየትኛው ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ በሕዝብ የተመረጠ ሕጋዊ መንግሥት እስካሁን ኖሮን ያውቃልና ነው፣ መጭው ምርጫ በሆነ ተዐምር ለሕዝባዊና ሕጋዊ መንግሥት መኖር እንደሚያበቃን አድርገን በርግጠኝነት የምንከራከረው? እንዲህ ዓይነቱ ክርክር ሕዝቡ ለውጥ እንዲመጣ የከፈለውን መሥዋዕትነት የመካድ ግብዝነት ከመሆን ያለፈ ትርጉም የለውም። እንዲያውም ከመጭው ምርጫ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው ዋናው ጥያቄ፥ 'ምርጫው ነጻና ፍትሐዊ ሆኖ የሕዝብ መንግሥት ሊያስገኝልን ይችላል ወይንስ አይችልም?' የሚል ሳይሆን፣ 'ቢያንስ የዛሬ አምስት ወይም ዐሥር ዓመታት እንደተካሄደው ምርጫ በአፈናና በተጽእኖ ተካሂዶ ሀገራችን ከህልውና አደጋ ልትተርፍ ትችላለች ወይ?' የሚል ነው።

ካለፈው የ19 ወራት የለውጥ ሒደት መረዳት እንደምንችለው "የለውጥ አመራሩ" በአሁኑ ወቅት በሕዝቡ ውስጥ ያለው ቅቡልነት የተመሠረተው በምርጫ የተመረጠ ሕጋዊ መንግሥት ስለሆነ ሳይሆን "የለውጥ አመራሩ" የሕዝቡን የለውጥ ጥያቄ በሕዝብ ትግል ተሸንፎ ስለተቀበለና የተሻለ ለውጥ አመጣለሁ ብሎ ቃል በመግባቱ ምክንያት የተገኘ ነው። "የለውጥ አመራሩ" ይህንን ሐቅ ከልቡ ተገንዝቦ ዋናውን ትኩረቱን በሕግና በፖለቲካ ትርጉም ጨዋታ ላይ ሳይሆን በለውጡ ሒደት ስኬታማነት ላይ ማድረግ ነበረበት። ይህንን ባለማድረጉም በሕዝብ ዘንድ የነበረው ቅቡልነት በከፍተኛ መጠንና ፍጥነት እያሽቆለቆለ ይገኛል።

“የለውጥ አመራሩ” በእስካሁኑ የ19 ወራት ሒደት የሠራው ትልቅ ስህተት ይህንን ታሪካዊ የሕዝብ አደራ በብቃት ለመወጣት ከመሞከር ይልቅ፣ የእርስ በርስ የፖለቲካ ሥልጣን ሽኩቻ ውስጥ በመግባት የራሱንም ሆነ የሀገሪቱን ወርቃማ ጊዜ ማባከኑ ነው። አሁንም ቁም ነገሩ ያለው የምርጫው መራዘም አለመራዘም ጉዳይ ላይ ሳይሆን፣ በምናራዝመው ጊዜ የሚቋቋመው የእርቅና የአንድነት የሽግግር መንግሥት እንዳለፈው 19 ወራት ጊዜውን እንደዋዛ ያባክነዋል ወይስ የለውጥ ሒደቱን በአስተማማኝ ሁኔታ ስኬታማ ለማድረግ በአግባቡ ይጠቀምበታል? የሚለው ነው። ጊዜውን በአግባቡ እስከተጠቀምንበት ድረስ የምርጫው ጊዜ መራዘሙ ለሀገራችን ህልውናና መጻኢ ዕድል እጅግ ጠቃሚ እንጂ ጎጂ ሊሆን አይችልም። ከዚህ ውጭ በሕግ መከበር አሳብቦ ሀገርን የማፍረስ አደጋ ወደ አረገዘ ምርጫ ውስጥ እንድንገባ መወትወት የሕግ ወገንተኝነት ሳይሆን ለሀገርና ለሕዝብ ደኅንነት ደንታ ቢስ መሆን ነው። ሕግ የሀገርንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል እንጂ ሀገርን ቀውስ ውስጥ ለማስገባት ጥቅም ላይ መዋል አይገባውምና።

## 1.7. የድህረ ምርጫ የሁነት ግምቶች /Scenarios/

የሆነ ሆኖ ገዥው ፓርቲ በተለመደ የመታበይ ባሕርይው በእንቢተኝነቱ ገፍቶበት መጭው ምርጫ በታሰበለት ጊዜ የሚካሄድ ከሆነ የሚከተሉት የሁነት ግምቶች /Scenarios/ ሊከሰቱ እንደሚችሉ ግምት አለን።

**ግምት** 1. ምርጫው ተካሂዶ በአንፃራዊነት ሰላማዊ፣ ነጻና ፍትሐዊ ሆኖ ይከናወናል። ይህ ከሆነ የእኛ ግምት ስህተት ይሆናል። ግምታችን ስህተት በመሆኑም ከማንም ያላነሰ ደስተኞች እንሆናለን።

**ግምት** 2. ምርጫው ተካሂዶ ግጭት፣ አፈናና ማጭበርበር የተሞላበት ሆኖ ይጠናቀቃል። የወቅቱ “የለውጥ ኀይልም” የለየለት አምባገነን ሆኖ በሥልጣን ላይ ይቀጥላል። ይህ ከሆነ ግምታችን ትክክል ነበር ማለት ነው። ነገር ግን በውጤቱ ባንደሰትም ያን ያህል አንከፋም። ሀገሪቷ ከመፍረስ ድናና በአገዛዝ ስር ሆና ህልውናዋ ከቀጠለ፣ ውጤቱን እየከፋንም ቢሆን እንደ አንድ ዕድል ልናየው እንችላለን።

**ግምት** 3. የምርጫው ሒደት መካሄድ ከጀመረ በኋላ በሚፈጠር ከአቅም በላይ በሆነ ብጥብጥ ከድምፅ መስጫው ዕለት በፊት ወይም በምርጫው ዕለት ምርጫው ሊቋረጥና በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ልንተዳደር የምንገደድበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። ይህ ከሆነም ‘ግምታችን ትክክል ነበር’ እንድንልና በእጅጉ እንድንከፋ ያደርገናል። ነገር ግን፥ በዚህ ሁኔታም የሀገሪቷ ህልውና መቀጠል ከቻለ መጽናኛ ይሆነናል።

**ግምት** 4. ምርጫው መካሄድ ከጀመረ በኋላ በማንኛውም ወቅት ላይ (ውጤቱ ከታወቀ በኋላ የምርጫውን ውጤት ባለመቀበልም ሊሆን ይችላል) ብጥብጥ ይፈጠራል። መንግሥት የተፈጠረውን ግጭትና ብጥብጥ መቆጣጠር ይሳነውና ሁኔታዎች ከቁጥጥር ውጭ ወጥተው ሀገር ወደ የእርስ በርስ ጦርነት ወይም መንግሥት የለሽ ሁኔታ ይገባል። ይህ ከሆነም በሚያሳዝን ሁኔታ ግምታችን ትክክል ነበር እንድንል ያደርገናል።

**ግምት** 5. ምርጫው ተካሂዶ በአንጻራዊነት ሰላማዊ ሆኖ ይጠናቀቃል። በምርጫው ውጤት መሠረትም አንድ ፓርቲ ብቻውን መንግሥት ለማቋቋም የሚያስችል ድምጽ ሳያገኝ ይቀርና ፓርቲዎች የጥምር መንግሥት ለማቋቋም ይገደዳሉ። የተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎችና አዲስ አበባም በተለያዩ ፓርቲዎች የሚተዳደሩበት ሁኔታ ይፈጠራል። የሀገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች በጋራ ሀገራዊ ጉዳዮቻቸው ላይ ብሔራዊ መግባባት ገና ስላልፈጠሩና በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሀገር የማስተዳደር ልምድና ብቃት ስለሌላቸው ወደ የእርስ በርስ ግጭት ይገቡና የተቋቋመው መንግሥት ይፈርሳል። የመንግሥት መፍረስንም ተከትሎ ሀገሪቱ ወደ የእርስ በርስ ብጥብጥ ወይም መንግሥት የለሽ ሁኔታ ውስጥ ትገባለች። ይህ ከሆነም በሚያሳዝን ሁኔታ ግምታችን ትክክል ይሆናል ማለት ነው።

ከእነዚህ አምስት የ'ይሆናል' ግምቶች በግልጽ እንደሚታየው ዐራቱ ግምቶች ከፍተኛ ሀገራዊ አደጋ ያዘሉ ናቸው። እነዚህ በስጋትነት የተገለጹ ዐራት ግምቶች የመከሰት ዕድላቸው ዝቅተኛ ነው የሚል ክርክር ሊቀርብ ይችል ይሆናል። ይህ ክርክር አሳማኝ ነው ብለን ባናምንም በተወሰነ ደረጃ እውነትነት ሊኖረው ከቻለ እንኳን ጉዳዩ የንግድ ወይም የሎተሪ ጉዳይ አይደለምና ይህንን ያህል የኪሳራ ግምት /Risk/ በሀገር ላይ መውሰድ ከባድ ስህተት ይሆናል። ምክንያቱም ከአሁን በኋላ በሀገራችን የሚካሄድ ምርጫ የተሳካ ካልሆነና ወደ እውነተኛ ዴሞክራሲ የሚያሸጋግረን ካልሆነ በስተቀር እንደገና ችግራችንን ሊፈታ የሚችል ሌላ የምርጫ ዕድል በቀላሉ ልናገኝ አንችልም። ከአሁን በኋላ የምናካሂደው ምርጫ እንዲሁ መደበኛ ምርጫ ሳይሆን አጠቃላይ የሀገሪቱን የወደ ፊት ህልውናና የመጭውን ትውልድ እጣ ፈንታ የሚወስን ስለሚሆን፣ ምርጫውን ማካሄድ ያለብን በግማሽ ልብና በብዙ ስጋት ውስጥ ሆነን ሳይሆን ምርጫውን ስኬታማ እንደምናደርገው ወደ ርግጠኝነት የተጠጋ ዝግጅት አድርገን መሆን ስላለበት ነው። በጥድፊያ የምንገባበት ምርጫ ምኞታችንን እስከ ወዲያኛው የሚያጨለም እንጂ የሚያሳካ ሊሆን አይችልም።

በእኛ በኩል እንዲሁ በስሜት ሳይሆን በሀገራችን በግልጽ ከሚታየው ነባራዊ ሁኔታና ከተጨባጭ የፖለቲካ ግምገማ ተነስተን መጭው ምርጫ መካሄድ የለበትም እያልን ነው። ሌሎች ደግሞ የምርጫው መካሄድ አዲስና የተለየ ነገር የሚፈጥርልን ይመስል ምርጫው የግድ መካሄድ አለበት እያሉ ነው። እነዚህ ኀይሎች እንደ ሀገር የምንገኝበትን አሳሳቢ ሁኔታ መረዳት የሚችሉት ምርጫው ውስጥ ተገብቶ የሀገርና የሕዝብ ንብረት ከወደመ፣ ዜጎች እርስ በርስ መገዳደል ከጀመሩ፣ ሀገሪቷም መፈራረስና መንግሥት የለሽ መሆን ከጀመረች በኋላ ይመስላል። በምኞት የሚሆን ነገር ካለ፥ የምንመኘው የእኛ ግምትና ግምገማ ስህተት ሆኖ የእነዚህ ግብዝ ኀይላት ተስፋና ምኞት እውን እንዲሆን ነው።

ስለሆነም በአሁኑ ወቅት የመንግሥት፣ የተቃዋሚ ፓርቲም ሆነ የምርጫ ቦርድ አካል ሆኖ ምርጫ መካሄድ አለበት ብሎ የወሰነና ይህንኑ የሚሰብክ ማንኛውም ድርጅትም ሆነ ሰው፥ በምርጫው ወቅት በሕዝብና በሀገር ላይ ሊደርስ ለሚችለው ማንኛውም ዓይነት ቀውስ እጅግ ከባድ ኀላፊነት እየወሰደ መሆኑን ከወዲሁ መገንዘብ አለበት። ኋላ ላይ ችግሩ ሲፈጠር ጣትን ወደ ሌላው አካል እየቀሰሩ 'እኔ ከደሙ ንጹሕ ነኝ' ማለት አይቻልም። ያኔ 'ችግሩ የተፈጠረው ሕገ መንግሥቱን ለማክበር ሲባል ነው' ብሎ መከራከርም የሚያዋጣ አይሆንም።

## 2. ምን ዓይነት የእርቅና የሽግግር መንግሥት? ለምንና እንዴት?

### መግቢያ

መጭው ምርጫ ለተወሰነ ጊዜ መራዘም አለበት የሚል አቋም ስናራምድ፣ ምርጫው በመራዘሙ ብቻ ምን አዲስ ነገር ሊፈጠር ይችላል? የሚል ጥያቄ ሊነሳ እንደሚችል መገመት ይቻላል። በተለይም የወቅቱ "የለውጥ አመራር" ከእንግዲህ የለውጥ ሒደቱን ውጤታማ የማድረግ አቅምም ሆነ ፍላጎት አለው ማለት አይቻልም የሚል ግምገማ ላይ በደረስንበት ሁኔታ የምርጫው ጊዜ በሚራዘምበት ወቅት ሊሰሩ የሚችሉት ሥራዎች በተጨባጭ ምንድን ናቸው? እነዚህን ሥራዎችስ በማንና እንዴት ሊሠሩ ይችላሉ? የሚሉ ጥያቄዎችም መነሳታቸው አይቀርም።

እርግጥ ነው፥ ምርጫው ይራዘም ሲባል ምርጫው የሚራዘመው እንዲሁ ጊዜ ወስዶ የሚሆነውን በዝምታ ለማየት ወይም በሥልጣን ላይ የሚገኘውን መንግሥት ዕድሜ ለማራዘም አይደለም። ይልቁንም ምርጫውን ማራዘም አስፈላጊ የሚሆነው የተጀመረውንና የመክሸፍ አደጋ የገጠመውን የለውጥ ሒደት ስኬታማ ለማድረግ፣ በሀገሪቱ ሰላምና የሕግ የበላይነትን ለማስፈንና ሀገሪቱን ከማንኛውም የውጭ ኀይሎች ጥቃት ለመከላከል የሚያስችሉ ሁኔታዎችን በአግባቡ ለመፍጠር ነው። ይህንን ከፍተኛ ኀላፊነት በአግባቡ ለመወጣት የሚቻለው ደግሞ ሁለት ዓመታት የተጠጋ ጊዜ ተሰጥቶት ይህንን ጊዜውን በአግባቡ መጠቀም ሳይችል ለቀረው የወቅቱ "የለውጥ አመራር" ሌላ ሁለተኛ ዕድል በመስጠት ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም "የለውጥ አመራሩ" የለውጥ ሒደቱን ውጤታማ የማድረግ አቅም ብቻ ሳይሆን ፍላጎትም እንደሌለው ላለፉት ሁለት ዓመታት በተግባር ታይቷል። "የለውጥ አመራሩ" ሀገሪቱን በሒደት ወደ ተሻለ አቅጣጫ ሳይሆን ወደ ባሰ ውስብስብ ችግር እያስገባት መሆኑ በገሃድ እየታየ ነው። ከእንግዲህ ከዚህ አመራር የባሰና ምናልባትም ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ሀገራዊ አደጋ እንጂ የተሻለ መፍትሔ መጠበቅ አይቻልም። ስለሆነም ከአሁን በኋላ የለውጥ ሒደቱን ስኬታማ ለማድረግ የሚቻለው በአዋጅ ሊቋቋም በሚችል በአንድ ሁሉን አቀፍ የእርቅና የአንድነት የሽግግር መንግሥት ነው።

የሽግግር መንግሥት ይቋቋም ሲባልም፥ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ እንዲህ ቀላል ሥራ ነው ወይ? የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኀይሎችስ ይህንን ኃላፊነት በአግባቡ የመወጣት ብቃት አላቸው ወይ? የሚሉ መሠረታዊ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ። የሽግግር መንግሥት ማቋቋም በእርግጥም ቀላል ሥራ አይደለም። በተለይም በእኛ ሀገር ተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታ እጅግ ፈታኝ ሥራ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። እንዲያውም ለአንድ ሀገር የፖለቲካ ችግር የሽግግር መንግሥትን የመሰለ አስቸጋሪ አማራጭ የለም። የዚህ የውይይት መነሻ ጽሑፍ አቅራቢ ዛሬ ራሴን የዚህ አማራጭ ሐሳብ ጠበቃ ሆኜ ስላገኘሁት በእጅጉ አዝናለሁ። ምክንያቱም የሽግግር መንግሥት ጥያቄ ከአንድ ሀገር መንግሥታዊ ሥርዓት ከፍተኛ ውድቀት የሚመነጭና በሌላ አማራጭ በቀላሉ የማይተካ መፍትሔ በመሆኑ ነው።

በእኛ በኩል የሀገራችንን የፖለቲካ ችግሮች ለመፍታት ከሽግግር መንግሥት በታች የሆነ ሌላ አማራጭ አለን ብለን ባመንበት ወቅት በግልጽ የሽግግር መንግሥት ጥያቄ ተቃዋሚ የሆነ አቋም ስናራምድ ቆይተናል። ለምሳሌ በሃያ ሰባት ዓመቱ የኢሕአዴግ የአገዛዝ ዘመን ቢያንስ አንፃራዊ ሰላምና የሕግ የበላይነት ማስከበር የሚችል ጠንካራ አምባገነናዊ መንግሥት በሥልጣን ላይ ስለነበር በሽግግር መንግሥት ሳይሆን በነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ሀገራችንን ወደ መዋቅራዊ ዴሞክራሲ የማሸጋገር ዕድል አለ ብለን እናምን ነበር። ዶ/ር አቢይ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ በነበሩት ጥቂት ወራቶች ደግሞ እነ ዶ/ር አቢይ ለውጥ ለማምጣት የተወሰነ ቁርጠኝነት ሊኖራቸው ይችላል የሚል ግማሽ ልብ የሆነ ተስፋ ስለነበረን ሀገራችን በሽግግር መንግሥት ሳይሆን በሽግግር ኮሚሽን አማካኝነት ወደ በጎ አቅጣጫ ልትሸጋገር ትችላለች የሚል እምነት ነበረን። ይህንን አቋማችንንም የሽግግር መንግሥት የማቋቋም ጥያቄ ተቃዋሚ ሆነን በግልጽ አራምደናል።

ነገር ግን እነዚህን ቀደም ሲል የነበርንበትን ነባራዊ ሁኔታ የሚመጥኑ ጥያቄዎች የቀድሞው ኢሕአዴግም ሆነ እነ ዶ/ር ዐቢይ በተገቢው ጊዜ ሊቀበሏቸው ባለመቻላቸው የሀገራችን ወቅታዊ ችግሮች የበለጠ ውስብስብ ወደ መሆን ተሸጋግረዋል። በወቅቱ እንደዚህ ዓይነት አቋም በማራመዳችን ባንጸጸትም፣ የወቅቱ የለውጥ አመራር ለውጡን ወደ ዘላቂ ስኬት የመቀየር አቅምም ሆነ ፍላጎት እንደሌለው በበቂ ጊዜና ግምገማ ካረጋገጥን በኋላ ግን ከእንግዲህ የወቅቱ የሀገራችን ችግር ሁሉን አቀፍ የእርቅና የሽግግር መንግሥት ከማቋቋም ባነሰ ሌላ አማራጭ እንደማይፈታ ተገንዝበናል።

በማንኛውም አካል የሚቀርብ ማንኛውም የመፍትሔ ሐሳብ ምንጊዜም ለውይይትና ለድርድር ክፍት መሆን እንዳለበት ቢታመንም፣ በእኛ በኩል ከዚህ በኋላ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም አንድ አማራጭ ብቻ ሳይሆን የግድ ልንተገብረው የሚገባ የመጨረሻ አማራጫችን ሆኗል ብለን አምነናል። አንድ ሀገርና ሕዝብ ከዚህ በታች በሆኑ አማራጮች ችግሩን መፍታት ካልቻለ ወደዚህ ዓይነቱ ከባድ አማራጭ ለመግባትና ይህንን ከባድ ኃላፊነት ለመወጣት ይገደዳል። ማንም ሀገር የተሻለ አማራጭ አጥቶና ከአቅም በላይ በሆኑ ሁኔታዎች ተገዶ እንጂ እንዲሁ በቀላሉ የሽግግር መንግሥት ወደ ማቋቋም አማራጭ ሊገባ አይችልም። እኛም ወደን ሳይሆን በሁኔታዎች አስገዳጅነት ይህንን ከባድ አማራጭ ለመምረጥ የወቅቱ ሁኔታ ያስገድደናል። ምክንያቱም ኢሕአዴግ የሚባለው ድርጅት የቱንም ያህል በጥልቅ እታደሳለሁ ብሎ ቢምልና ቢገዘት፣ የቱንም ያህል አደረጃጀቱንና መሪዎቹን ቢቀያይር መቼም ጊዜ ቢሆን መሠረታዊ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል ድርጅት አለመሆኑን ደጋግሞ አረጋግጦልናል። አጉል ተስፈኞች ብቻ ሳይሆን ቂሎች ካልሆንን በስተቀር ከእንግዲህ የኢሕአዴግ ቅሪት አካል በሆነው በብልጽግና ፓርቲ ተመርተን የሚጠብቀን ዕድል ለይቶልን መፈራረስ ካልሆነ በስተቀር ወደ በጎ አቅጣጫ መሸጋገር ሊሆን አይችልም።

የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ከባድ ሥራ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በእኛ እምነት ከሌሎች ተመሳሳይ ችግር ከገጠማቸው ሀገራትም ሆነ ካለፉት የሀገራችን የሽግግር ወቅቶች ጋር ሲነጻጸር ግን የሽግግር መንግሥት ለማቋቋም የሚያስችል የተሻለ ሁኔታ ዛሬ በሀገራችን በሚከተሉት ሁለት ምክንያቶች አለ ብለን እናምናለን።

አንደኛ፥ ምንም እንኳ የወቅቱ የሀገራችን ፖለቲካ ጽንፈኝነትና ብሔርተኝነት አብዝቶ ያጠላበት ቢሆንም በአሁኑ ወቅት በጎላ ሁኔታ የታጠቀ ሠራዊት ያለው ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት አለመኖሩ አንድ ምቹ ሁኔታ ነው። ቢያንስ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በአሁኑ ወቅት በአንድ አዳራሽ ውስጥ ፊት ለፊት ተገናኝተው ለመነጋገር የሚያቀርቡት ቅድመ ሁኔታ የለም። ብዙውን ጊዜ በብዙ ሀገራት የሽግግር መንግሥት ለማቋቋም ሲሞከር ከባድ ችግር ሲሆን የሚታየው የዚህ ዓይነቱ የፖለቲካ ሁኔታ ዛሬ በሀገራችን አለመኖሩ አንድ ጥሩ አጋጣሚ ተደርጎ ሊታይ ይችላል።

ሁለተኛ፥ በብዙ ሀገራትም ሆነ በእኛ ሀገር ያለፈ ታሪክ እንዳየነው ብዙውን ጊዜ የሽግግር መንግሥት የሚቋቋመው አንድ መንግሥት በሌላ አዲስ ኀይል በትጥቅ ትግል ወይም በአብዮት ተሸንፎ ሲተካ፣ ወይም በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት በራሱ የውስጥ ችግር ሙሉ በሙሉ ሲፈርስ ነው። ለምሳሌ የአረብ ስፕሪንግ በመባል የሚታወቀው አብዮት የተካሄደባቸው ሀገራት የሽግግር መንግሥት ለማቋቋም የተገደዱት በሥልጣን ላይ የነበሩት መንግሥታት በአብዮት በመፈራረሳቸው ነው። በቅርቡ የሀገራችን የፖለቲካ ታሪክ የተከሰቱትን የሽግግር መንግሥታት ካየንም፥ በደርግ ወቅት የተቋቋመው የሽግግር መንግሥት የንጉሡ ሥርዓት በተካሄደው ስር ነቀል አብዮት ምክንያት ሙሉ በሙሉ በመፍረሱ፤ በኢሕአዴግ ጊዜ የተቋቋመው የሽግግር መንግሥት ደግሞ የደርግ መንግሥት ሙሉ በሙሉ በጦርነት በተካሄደ ትግል በመፍረሱ ምክንያት ነው የተቋቋመው። እነዚህ የሽግግር መንግሥታት ለሀገሪቱ ዘላቂ መፍትሔ ሳያመጡ ቢቀሩም ሽግግሮቹ ግን በወቅቱ የሀገርን ህልውና አደጋ ውስጥ ሳያስገቡ መጠናቀቅ ችለው ነበር።

በአሁኑ የሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ግን መንግሥት በሌላ አዲስ መንግሥት አልተተካም። መንግሥትም በአግባቡ ሕግና ሥርዓትን ማስፈን በማይችልበት ደረጃ ተልፈሰፈሰና ተዳከመ እንጂ “መንግሥት የለም” በሚያስብል ደረጃ እስካሁን ገና አልፈረሰም። እነዚህ ሁኔታዎች ኢትዮጵያ የተሳካ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም እንድትችል የተሻለ ምቹ ሁኔታዎች የሚፈጥሩ ናቸው። በእኛ እምነት አሁን እነዚህ በጎ እርሾዎች ባሉበት ሁኔታ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ካልቻልን ከዚህ የባሰና ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ሁኔታ ውስጥ ከገባን በኋላ ግን ይህንን ዕድል መልሰን ልናገኘው አንችልም። አሁን በሥልጣን ላይ ያለው ደካማ መንግሥት ጭራሹኑ ፈራርሶ አንድ ጊዜ መንግሥት የለሽ ሁኔታ ውስጥ ከገባን፣ በየመንና በሊቢያ እንደታየው ወደ እልቂትና ፍጅት ውስጥ የመግባት እንጂ የሽግግር መንግሥት ለማቋቋምም ሆነ በሌላ አማራጭ ሀገሪቷን ከጥፋት ለመታደግ የምንችልበት ዕድል አይኖርም።

የወቅቱ “የለውጥ ኀይል” ይህንን እውነታ ተገንዝቦ የሽግግር መንግሥት የማቋቋም ጥያቄን ቢቀበል ሒደቱን ስኬታማ በማድረግ ረገድ ቁልፍ ሚና ሊጫወት ይችላል። ምክንያቱም አሁን እየቀረበ ያለው የሽግግር መንግሥት ጥያቄ ገዢውን ፓርቲ ሙሉ በሙሉ ከሥልጣን አስወግዶ በአዲስ መንግሥት የሚተካ ሳይሆን የገጠመንን ሀገራዊ የህልውና ጥፋት ለመታደግ መንግሥት ብቻውን ሳይሆን ከሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎችና የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር አብሮ ሊሰራ የሚችልበት ሁሉን አቀፍ የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም የሚጠይቅ ነው። የወቅቱ “የለውጥ ኀይል” ይህንን ጥያቄ ቢቀበል በዋናነት ሀገሪቱን ከህልውና አደጋ ለመታደግ፣ ከዚህ በተጨማሪም ራሱን ከመፈራረስ አድኖ በወደፊቱ የሀገሪቱ የፖለቲካ ሒደት በምርጫ አሸናፊ ሆኖ በሥልጣን ላይ ለመቀጠል የሚያስችል ዕድል ሊኖረው ይችላል። ይህንን ጥያቄ መቀበል ብልህነትና አሸናፊነት እንጂ ከቶውንም ሞኝነትና ሽንፈት ተደርጎ ሊቆጠርም

አይገባውም። በርግጥም ብልጽግና ፓርቲ አራምደዋለሁ የሚለው "የመደመር" አስተሳሰቡ፥ ከአንገት ሳይሆን ከአንጀት ከሆነ ይህንን አማራጭ መቀበል ይኖርበታል። "እኔ አሻግራችኋለሁ" የሚለው አስተሳሰብ ሌሎችን ከመቀነስ ጋር እንጂ ከመደመር ጋር አብሮ አይሄድም። በዚህ ሒደት አንዳችን አሻጋሪ፣ ሌላችን ተሻጋሪ ሳይሆን ሁላችንም አሻጋሪና ተሻጋሪ መሆን ይኖርብናል። ዴሞክራሲ የውጤት ብቻ ሳይሆን የሒደትም ጉዳይ መሆኑ በትክክል ገብቶን ከሆነ "እኔ አሻግራችኋለሁ" የሚለው አስተሳሰብ የዴሞክራሲ ተጻራሪ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ይልቁንም እውነተኛው የመደመር ተግባር ሁሉን አቀፍ የእርቅና የአንድነት የሽግግር መንግሥት የማቋቋምን ጥያቄን መቀበል ነው።

በዚህ ላይ መግባባት ከቻልን ቀጥሎ ሊመጣ የሚችለው ጥያቄ፣ ሊቋቋም የሚችለው የሽግግር መንግሥት እንዴትና በእነማን ሊቋቋም ይችላል? ከተቋቋመ በኋላስ የሚተገብራቸው ኀላፊነቶችና የሚያሳካቸው ዐላማዎች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ? የሚል ይሆናል።

እነዚህን ጥያቄዎች በተመለከተ በእኛ በኩል ያለንን አመለካከትና ለውይይት መነሻ ሊሆን ይችላል ብለን የምናምንበትን ሐሳብ በጥቅሉ እንደሚከተለው እናቀርባለን። በመጨረሻም፥ ይህ የመነሻ ሐሳብ አንዳችንን አሸናፊ፣ ሌላችንን ተሸናፊ በማድረግ አዙሪት ውስጥ ለማስቀጠል ሳይሆን ሁላችንንም አሸናፊ ለማድረግ በሚያስችል አግባብና ሀገራችንን ከገባችበት የፖለቲካ አጣብቂኝ ለማውጣት ታስቦ የተዘጋጀና ለውይይት የቀረበ መነሻ ሐሳብ ነው። ስለሆነም መነሻ ሐሳቡን ስናነብብ ራሳችንን ከግልና ከቡድን ጠባብ የፖለቲካ አመለካከት አርቀን የሀገርንና የሕዝብን ጥቅም በሚያስቀድም አግባብ እንድንረዳውና ገንቢ ምላሽ እንድንሰጥበት ያስፈልጋል።

## 2.1. ሀገራዊ የውይይት ሒደት /National Dialogue/

ምን ዓይነት የእርቅና የሽግግር መንግሥት እንደሚያስፈልገን በዝርዝር መወሰን ያለበት ረዘም ላለ ጊዜ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የተለያዩ ባለ ድርሻ አካላት በሚያካሂዱት ሀገራዊ የውይይት ሒደት ሊሆን ይገባዋል። ለምሳሌ ምርጫው እንዲራዘም መስማማት ላይ መድረስ ከቻልን ይህ ሀገራዊ የውይይት ሒደት ከአሁን ጀምሮ እስከ መስከረም 30 ቀን 2013 ዓ.ም. ሊካሄድ ይችላል። ይህንን ሀገራዊ የውይይት ሒደት አንድ ገለልተኛ የሆነ የተጽእኖ ፈጣሪ ግለሰቦች ጥምረት፣ ወይም አንድ ከሲቪክ ማኅበራትና የሃይማኖት ተቋማት የተውጣጣ ጥምረት ሊያካሂደው ይችላል። ሒደቱን የሚመሩት አካላት እነማን ሊሆኑ ይገባል? የሚለው ይህ ጥያቄም በገዢው ፓርቲና በተቃዋሚ ፓርቲዎች ድርድር ሊወሰን ይችላል። እኛ ከዚህ በታች የምናቀርበው ሐሳብ ምን ዓይነት የሽግግር መንግሥት ሊቋቋም እንደሚችል አጠቃላይ አቅጣጫ ለማሳየት የቀረበ እንጂ እንዲህ ዓይነቱ ጥያቄ መልስ ማግኘት ያለበት በአንድ ፓርቲ ወይም መንግሥት ሳይሆን ሁሉን አቀፍ በሆነ ሀገራዊ የውይይት ሒደት /National Dialogue/ መሆን ይገባዋል።

## 2.2. የሚቋቋመው የሽግግር መንግሥት ስያሜ ምን ይሁን?

የሚቋቋመው የሽግግር መንግሥት ስያሜ "የኢትዮጵያ ሕዳሴ የእርቅና የአንድነት የሽግግር መንግሥት" በአጭሩ "የህዳሴ መንግሥት" ተብሎ ቢጠራ ተገቢ ይሆናል። ይህ ሕዳሴን፣ እርቅን፣ አንድነትንና ሽግግርን ያጣመረ ስያሜ አስፈላጊና ተገቢ የሚሆነውም ከሚከተለው የሽግግር መንግሥቱ ዋና ዋና ዐላማዎች ጋር በተያያዘ ይሆናል።

## 2.3. የሽግግር መንግሥቱ ዐላማ ምንድን ነው?

የሚቋቋመው የእርቅና የሽግግር መንግሥት አምስት ዋና ዋና ዐላማዎች ይኖሩታል። የመጀመሪያው፥ በሀገሪቱ ብሔራዊ እርቅ እንዲወርድና የሽግግር ጊዜ ፍትሕ /Transitional Justice/ እንዲሰፍን ማድረግ ይሆናል። ሁለተኛ፥ የሀገሪቱ የፖለቲካ ኀይሎች በመካከላቸው ባሉ መሠረታዊ የፖለቲካ ቅራኔዎች ዙሪያ ድርድር አካሂደው በዋና ዋና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ አንጻራዊ ብሔራዊ መግባባት እንዲፈጥሩ ማስቻል ይሆናል። ሦስተኛ፥ በሀገሪቱ ሰላምና የሕግ የበላይነትን በማስፈን ሀገሪቱን ከገጠማት የፖለቲካ ቀውስ መታደግ ይሆናል። ዐራተኛ፥ ከሕዳሴ ግደብ ጋር በተያያዘ የሚገጥማትን ውጫዊ ጫና መቋቋምና ሕዳሴ ግድብን ለፍጻሜ ማብቃት ይሆናል። አምስተኛ፥ በእነዚህ ዐላማዎች የተገኙትን ውጤቶች መሠረት አድርጎ ሀገራችን ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰላማዊ፣ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ አካሂዳ ሀገራችን የሕዝብ መንግሥት ለማቋቋም እንድትበቃ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይሆናል።

## 2.4. የሽግግር መንግሥቱ የሥራ ዘመን ምን ያህል ይሆናል?

የሽግግር መንግሥቱ የሥራ ዘመን ሁለት ዓመታት፣ ማለትም ከመስከረም 30 ቀን 2013 ዓ.ም. እስከ መስከረም 30 ቀን 2015 ዓ.ም. ድረስ ይሆናል። ከነዚህ ሁለት የሽግግር ዓመታት ውስጥ፥ በመጀመሪያው ዓመት ሰላምና የሕግ የበላይነትን በመላው ሀገሪቱ ለማስፈን፣ ብሔራዊ እርቀ ሰላም ለማውረድና የሽግግር ጊዜ ፍትሕ ለመስጠት ትኩረት ይደረጋል። በሁለተናው ዓመት ደግሞ፥ የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ረቂቅ ለማዘጋጀትና የምርጫ ዝግጅት ለማድረግ የበለጠ ትኩረት ይሰጣል። ነገር ግን ሀገሪቱ ከምትገኝበት ውስብስብ ችግሮች አኳያ ሁለት ዓመት በጣም አጭር ጊዜ በመሆኑ ሁሉም የሽግግር መንግሥቱ ኀላፊነቶች የሽግግር መንግሥቱ ከሚቋቋምበት ዕለት ጀምሮ በከፍተኛ ፍጥነትና ርብርብ መሠራት ይኖርባቸዋል።

## 2.5. የሽግግር መንግሥቱ በማንና እንዴት ይቋቋማል?

የሽግግር መንግሥቱ የሚቋቋመው የሀገራዊ የውይይት ሒደቱን መሠረት ባደረገ አዋጅ ይሆናል። የአዋጁ ረቂቅ የሚዘጋጀው ገዥው ፓርቲና ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሀገራዊ የውይይት ሒደቱ ወቅት በሚያደርጉት ድርድር ሲሆን፣ አዋጁን የሚያጸድቀውና የሽግግር መንግሥቱን በይፋ የሚያቋቁመው በአሁኑ ወቅት በሥራ ላይ ያለው የሀገሪቱ ፓርላማ ይሆናል።

እዚህ ላይ ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ፣ ከመቶ በላይ የሆኑት የሀገሪቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዴት ሥርዓት ባለው ሁኔታ ተደራድረው አዋጁን ሊያረቁ ይችላሉ? ከዚያ በኋላ በሚኖረው የሽግግር ሒደትስ በምን ዓይነት አግባብ የሥልጣን ክፍፍል አድርገውና ሥርዓት ባለው መንገድ እየተደራደሩ ሽግግሩን ውጤታማ ሊያደርጉት ይችላሉ? የሚል ይሆናል።

በእኛ አመለካከት የሽግግር ሒደቱ ዋና ተዋናይ መሆን ያለባቸው ሦስት አካላት ናቸው። እነሱም ገዥው ፓርቲ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ኅብረተሰቡን በተለያየ መንገድ ሊወክሉ የሚችሉ ግለሰቦች ናቸው። ገዥው ፓርቲ ራሱንና በአሁኑ ወቅት በሥልጣን ላይ የሚገኘውን መንግሥት ወክሎ በሒደቱ አንድ ተዋናይ ይሆናል። ተቃዋሚ ፓርቲዎች በቁጥር በርካታ ስለሆኑ በሒደቱ ሥርዓት ባለው መንገድ ተዋናይ ለመሆን እንዲችሉ በቅድሚያ አንድ ዓይነት የጋራ አደረጃጀት መፍጠር ይኖርባቸዋል።

ይኸውም፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ትርጉም ባለውና ሥርዓት ባለው መንገድ እስከ መጪው መስከረም 30 ቀን 2013 ዓ.ም. በሚካሄደው ሀገራዊ የውይይት ሒደትም ሆነ ለሁለት ዓመታት በሚቆየው የሽግግር ሒደት በአግባቡ ተዋናይ እንዲሆኑ አስቀድመው ራሳቸውን በሁለት ጎራ ከፍለው ማደራጀት ይኖርባቸዋል። ተቃዋሚ ፓርቲዎች ራሳቸውን በሁለት ጎራ ከፍለው ለማደራጀት የሚጠቀሙበት መስፈርትም መሠረታዊ የፖለቲካ ቅራኔያቸው በሚገለጽበት፣ ማለትም የወቅቱን ሕገ መንግሥት በሚመለከት ባላቸው አቋም ሊሆን ይገባል። ይኸውም በአንድ በኩል የወቅቱ ሕገ መንግሥት በዋናነት የአፈጻጸም እንጂ የይዘት ችግር የለበትም ብለው የሚያምኑ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በአንድ ጎራ ተቧድነው ይደራጃሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ሕገ መንግሥቱ የአፈጻጸም ብቻ ሳይሆን መሠረታዊ የይዘት ችግር አለበት ብለው የሚያምኑ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሁለተኛ ጎራ ሆነው በመቧደን ይደራጃሉ። ሆኖም 'የሕገ መንግሥቱ መሻሻልም ሆነ ባለበት የመቀጠል ጉዳይ ቀዳሚ አጀንዳዬ አይደለም' የሚል ፓርቲ ካለ በሌሎች አጀንዳዎች ይቀርበኛል ወደሚለው ጎራ መርጦ የመቀላቀል መብት ይኖረዋል።

ይህ መሆን ከቻለ፣ በአጠቃላይ የሀገሪቱ ፓርቲዎች በሦስት ጎራ ይከፈላሉ ማለት ነው። ገዥው ፓርቲ ራሱን ችሎ "ጎራ አንድ" ሲሆን፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከፍ ሲል በተጠቀሰው የልዩነት መስፈርት ለሁለት ተከፍለው፣ "ጎራ ሁለት" እና "ጎራ ሦስት" ይሆናሉ ማለት ነው።

በሌላ አባባል በፓርቲዎች መካከል የሚደረግ ማንኛውም ድርድር የሦስት ጎራ ወይም የሦስትዮሽ ድርድር ይሆናል ማለት ነው። ከመቶ በላይ የሆኑ ፓርቲዎች ራሳቸውን ችለው በአንድ የሽግግር ሒደት በሥርዓት ሊወከሉና ሊደራደሩ የሚችሉበት ዕድል ስለማይኖር የሽግግር መንግሥቱ እንዲቋቋም መስማማት ላይ ሲደረስ ተቃዋሚዎች ይህንን አደረጃጀት ፈጥረው የጋራ ወኪል እየመረጡ በሒደቱ በሚፈጠሩ መዋቅሮች በአግባቡ መወከልና ሥርዓት ባለው መንገድ መደራደር ይችላሉ ማለት ነው። ይህንን ማድረግ ቀላል ሥራ ባይሆንም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከራሳቸው የፓርቲ የሥልጣን ጥያቄ በላይ የሀገሪቱን ህልውናና ጥቅም የሚያስቀድሙ ከሆነ በዚህ መልክ የግድ ራሳቸውን አድራጅተው መቅረብ ይኖርባቸዋል።

ገዢው ፓርቲ ከራሱ ሥልጣን በላይ የሀገሪቱን ጥቅም አስቀድሞ የሽግግር መንግሥት የማቋቋሙን ጥያቄ ለመቀበል ከወሰነ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም በበኩላቸው ይህንን አደረጃጀት ተቀብለው ለመደራደር መወሰን ይጠበቅባቸዋል። ይህንን አደረጃጀት የማይቀበል ተቃዋሚ ፓርቲ በፓርቲነት የመቀጠልና ወደ ፊት በሚካሄደው ሀገራዊ ምርጫ የመሳተፍ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ነገር ግን የሽግግር መንግሥቱ አካል አይሆንም። ይህ ጥረት ተሳክቶ በሦስት ጎራ የተከፈሉት ፓርቲዎች በሽግግር ሒደቱ ወቅት በትብብር አብሮ የመሥራት ባሕልን መለማመድና ማዳበር ከቻሉም በወደፊቱ የሀገራችን የመድብለ ፓርቲ ፖለቲካ የኅብረተሰቡን ጥቅምና ፍላጎት በአግባቡ መወከል የሚችሉ ሦስት ጠንካራ ሀገራዊ ፓርቲዎች ተጠናክረው እንዲወጡ ለማድረግ ሊያግዝ ይችላል። ከገዥው ፓርቲና ከተቃዋሚ ፓርቲዎች በተጨማሪ በሒደቱ ውስጥ ሦስተኛ ተዋናይ ሊሆኑ የሚችሉት ከፖለቲካ አደረጃጀት ውጭ የሆኑና ኅብረተሰቡን በተለያየ መንገድ የሚወክሉ ግለሰቦች ናቸው።

እነዚህ ሰዎች ከሲቪልና ብዙኃን ማኅበራት፣ ከሃይማኖት ድርጅቶች፣ ከሀገር ሽማግሌዎች፣ ከዲያስፖራው ማኅበረሰብ፣ ከምሁራንና በተለያየ መንገድ ተጽእኖ ፈጣሪ ከሆኑ ግለሰቦች የተውጣጡ ይሆናሉ። ስለዚህ የእርቅና የሽግግር መንግሥቱ ተዋናዮች እነዚህ ሦስት ዋና ዋና አካላት፣ ማለትም ገዥው ፓርቲ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች (ለሁለት ተከፍለው) እና ከፍ ሲል የተዘረዘሩት ከፖለቲካ አደረጃጀት ውጭ የሆኑ የግለሰቦች ስብስብ ናቸው ማለት ነው። ከሦስቱ የፖለቲካ ፓርቲ ጎራዎች በተጨማሪ ይህ የግለሰቦች ስብስብም እንደ አንድ ጎራ ራሱን አደራጅቶና የራሱን መሪዎች መርጦ በሽግግሩ ወቅት በሚካሄዱ ድርድሮች ተሳታፊ ይሆናል። እነዚህ የግለሰብ ስብስቦች የሚሳተፉባቸው የድርድር ሒደቶች ግን በውስን ጉዳዮች ላይ ይሆናሉ። ስለሆነም በሽግግር ሒደቱ ወቅት የሚካሄዱት ድርድሮች፥ አንዳንድ ጊዜ የሦስትዮሽ (ማለትም የፓርቲዎች ብቻ)፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የዐራትዮሽ (ማለትም የግለሰቦችን ስብስብ ጨምሮ) የሚሆኑበት ዕድል ይኖራል ማለት ነው።

## 2.6. የሽግግር መንግሥቱ ዐላማውን ለማሳካት ምን ምን ተግባራትን ያከናውናል?

የእርቅና የአንድነት የሽግግር መንግሥቱ፣ ዐላማውን በብቃት ለማሳካት በአዋጅ ተዘርዝረው የሚሰጡትን የሚከተሉትን አምስት ዋና ዋና ተግባራትና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን ያከናውናል።

***አንደኛ፥*** የሀገሪቱን የመንግሥት /የሚኒስትር መስሪያ ቤቶችን/ የዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴ ያከናውናል፤

***ሁለተኛ፥*** በሀገሪቱ ሰላምና የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን የሚያደርጉና ሀገሪቱን ከማንኛውም የውጭ ጥቃት ለመከላከል የሚያስችሉ ተግባራትን ያከናውናል፤

***ሦስተኛ፥*** በሀገሪቱ እርቀ ሰላምንና የሽግግር ጊዜ ፍትሕን ለማስፈን የሚያስችሉ ተግባራትን ያከናውናል፤


***ዐራተኛ፥*** የፖለቲካ ፓርቲዎችን ድርድር መሠረት ያደረጉ የሕግና የተቋማት የማሻሻያ ሥራዎችን በመሥራት ብሔራዊ መግባባትን ይፈጥራል፤

***አምስተኛ፥*** በሀገሪቱ ሰላማዊ፣ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ የሚካሄድበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤

## 2.7. የሽግግር መንግሥቱ ምን ዓይነት አደረጃጀት ወይም መዋቅር ይኖረዋል?

የሽግግር መንግሥቱ በአዋጅ ተደንግገው የተሰጡትን ዐላማዎች ለማሳካትና ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ዝርዝር ኀላፊነቶቹን በአግባቡ ለመተግበር የሚከተለውን መዋቅር መሠረት አድርጎ ይደራጃል።

### የኢትዮጵያ ህዳሴ የእርቅና የአንድነት የሽግግር መንግሥት መዋቅር



### 2.7.1. የህዳሴ ሸንጎ

ከላይ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ይህ ሀገር አቀፍ የህዳሴ ሸንጎ በአሁኑ ወቅት በሥራ ላይ ባለው ፓርላማ በአዋጅ የሚቋቋም ሲሆን ለመጪዎቹ ሁለት ዓመታት ፓርላማውን ተክቶና ትልቁ የሀገሪቱ የሥልጣን አካል ሆኖ ሀገሪቱን የሚመራ ሸንጎ ይሆናል። የፌደራሉ ፓርላማና የክልል ምክር ቤቶች በነጻና ፍትሐዊ ምርጫ ተቋቁመው ከሽግግር መንግሥቱ ሥልጣን እስከሚረከቡ ድረስ ሸንጎው በመላው ሀገሪቱ ብቸኛ ሕግ አውጭ አካል ሆኖ ያገለግላል። ይህ ሸንጎ 505 አባላት የሚኖሩት ሲሆን፣ ከእነዚህ አባላት ውስጥ 150 አባላት ከገዥው ፓርቲ፣ 150 አባላት በሁለት ጎራ ከተከፈሉት ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ 150 አባላት ከልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከሚመረጡት ግለሰቦች፣ 55 አባላት ከዘጠኙ ክልሎችና ከሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች ተወጣጥተው የሚወከሉ ይሆናሉ።

እነዚህ የሸንጎ አባላት የሚመረጡት በገዥው ፓርቲና በተቃዋሚ ፓርቲዎች የሦስትዮሽ ድርድር ሲሆን የሸንጎ አባልነታቸው የሚጸድቀው ግን ሸንጎውን የማቋቋም ሥልጣን በሚኖረው ፓርላማ ይሆናል። በሸንጎው ውስጥ ዘጠኙ የሀገሪቱ ክልሎችና ሁለቱ የፌደራል ከተሞች እያንዳንዳቸው በቀጥታ ከሚወከሏቸው አምስት አምስት ተወካዮች በተጨማሪ በሁሉም ተደራዳሪ ጎራዎች ውስጥም ተገቢ ውክልና እንዲኖራቸው ይደረጋል። ሴቶችና ወጣቶችም በአግባቡ እንዲወከሉ ይደረጋል።

ሸንጎው ሥልጣኑን ከወቅቱ ፓርላማ ተረክቦ የሚቋቋመው መስከረም 30 ቀን 2013 ዓ.ም. ሲሆን በተቋቋመበት ዕለት አፈ ጉባኤውንና ምክትል አፈ ጉባኤውን ይመርጣል። የሚመረጡት ሁለቱ አፈ ጉባኤዎች የፓርቲ አባል ያልሆኑ የሸንጎው አባላት ይሆናሉ። ሸንጎው በተቋቋመ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሁለት ዓመታት የሥራ ዕቅዱንና የራሱን የውስጥ አሠራር ሥነ ሥርዓት በዝርዝር አውጥቶ ያጸድቃል፤ ለሁለት ዓመቱ የሽግግር ጊዜ ለሽግግር መንግሥቱ በአዋጅ የተሰጡ ኀላፊነቶችን የመፈጸም ሥልጣን የሚኖረው አንድ የሽግግር ጊዜ የሥራ አስፈጻሚ ካውንስል ያቋቁማል። ሁሉም የክልል ምክር ቤቶች ተመሳሳይ የክልል የሽግግር ጊዜ የሥራ አስፈጻሚ ካውንስል አቋቁመው እንዲበተኑ ይደረጋል።

የህዳሴ ሸንጎው የሀገሪቱ ርእሰ ብሔር የሽግግር ዘመኑም ርእሰ ብሔር ሆነው በኀላፊነታቸው እንዲቀጥሉ ይወስናል። ከሽግግር መንግሥቱና በሽግግር መንግሥቱ አማካኝነት የሚቋቋሙ ተቋማት ኀላፊነቶችን ከሚመለከቱ ጉዳዮች ውጭ በአሁን ወቅት በሥራ ላይ ያሉ ሕግጋትና ተቋማት በሙሉ የሽግግር ዘመኑም ሕግጋትና ተቋማት ሆነው ይቀጥላሉ። ሸንጎው የሽግግር መንግሥቱን ኀላፊነት በአግባቡ ለመወጣት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘውም በሽግግሩ ወቅት ከሰላምና መረጋጋት ጋር የተያያዙ አንዳንድ የፖለቲካ መብቶች ላይ ጊዜያዊ እገዳ እንዲጣል ማድረግ የሚያስችል ዐዋጅ ሊያወጣ ይችላል። በማዕከል ደረጃ ከሚቋቋሙ የሽግግር መንግሥቱ መዋቅሮችና በክልል ደረጃ ሽግግሩን በበላይነት ለማስፈጸም በክልል ምክር ቤቶች ከሚቋቋመው የክልል የሽግግር ጊዜ የሥራ አስፈጻሚ ካውንስል ውጭ ያሉ የሀገሪቱ መንግሥታዊ መዋቅሮች በሙሉ ሳይፈርሱ በሥራ ላይ እንዲቀጥሉ ይደረጋል።

### 2.7.2. የሥራ አስፈጻሚ ካውንስል

የሽግግር መንግሥቱ የሥራ አስፈጻሚ ካውንስል በሸንጎው የሚቋቋምና ተጠሪነቱም ለሸንጎው የሆነ የሽግግር መንግሥቱ ሥራ አስፈጻሚ ነው። ካውንስሉ 30 አባላት የሚኖሩት ሲሆን እነዚህ አባላቱ ዐሥሩ ከገዥው ፓርቲ፣ ዐሥሩ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ ዐሥሩ ከሌሎች የሸንጎው አባላት የሚወከሉበት ይሆናል። የካውንስሉ አባላት ሹመት የሚጸድቀው በሸንጎው ቢሆንም የሚመረጡት ግን በገዥው ፓርቲና በተቃዋሚ ፓርቲዎች የሦስትዮሽ ድርድር ይሆናል።

ካውንስሉ በፓርቲዎች የሦስትዮሽ ድርድር መሠረት አንድ የሽግግር ዘመን ዋና ጠቅላይ ሚኒስትርና ሁለት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮች የሚመርጥ ሲሆን፣ ዋናው ጠቅላይ ሚኒስትር አሁን በሥልጣን ላይ ካለው ገዢ ፓርቲ፣ ሁለቱ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮች ደግሞ ከሁለቱ የተቃዋሚ ጎራዎች የሚመረጡ ይሆናል። እነዚህ የካውንስሉ ሦስት ጠቅላይ ሚኒስትሮች የእርስ በርስ ድርድር አካሂደው የሽግግር መንግሥቱን አምስት ዋና ዋና ኃላፊነቶች በአግባቡ ማስፈጸም የሚችሉ አንድ ካቢኔና አምስት ኮሚሽኖችን ያቋቁማሉ። እነሱም የሚኒስትሮች ካቢኔ፣ የክልሎች የሽግግር አስተባባሪ ኮሚሽን፣ የብሔራዊ ደኅንነት አስከባሪ ኮሚሽን፣ የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ረቂቅ ሐሳብ አቅራቢ ኮሚሽን፣ የእርቀ ሰላምና የሽግግር ጊዜ ፍትሕ አስፈጻሚ ኮሚሽን፣ የነጻና ፍትሐዊ ምርጫ አመቻች ኮሚሽን ናቸው። እነዚህ ኃላፊነቶች በተቀመጡበት ቅደም ተከተል የመጀመሪያዎቹ ሦስት ኃላፊነቶች በፖለቲካ ፓርቲ አባላት (በሦስቱ ጠቅላይ ሚኒስትሮች)፣ ቀሪዎቹ ሦስት ኃላፊነቶች ደግሞ የፖለቲካ ፓርቲ አባል ባልሆኑ ሌሎች የሥራ አስፈጻሚ ካውንስሉ አባላት (ከግለሰቦች ስብስብ) የሚመሩ ይሆናል።

### 2.7.3. የሚኒስትሮች ካቢኔ

የዚህ የሽግግር ጊዜ ካቢኔ ዋና ኃላፊነት አሁን በሥራ ላይ ባሉት የሚኒስትር መስሪያ ቤቶች ኃላፊነት ስር የሚሠሩ የመንግሥት መደበኛ የዕለት ተዕለት ሥራዎችን መሥራት ይሆናል። የፖለቲካ ሥራዎች በዋናነት በሽግግር መንግሥቱ ሌሎች መዋቅሮች የሚሠሩ ስለሚሆን የካቢኔው ዋና ትኩረት በሽግግሩ ወቅት ጤናማ የኢኮኖሚ የሥራ ሒደትና እድገት በሀገሪቱ እንዲኖር ለማድረግ ይሆናል። የህዳሴን ግድብ ሥራ የማፋጠን ጉዳይም የዚህ ካቢኔ ኃላፊነት ይሆናል። የዚህ ካቢኔ ሰብሳቢና አደራጅ ዋናው ጠቅላይ ሚኒስትር ሲሆን ለካቢኔ አባልነት በሚሰጣቸው ሹመቶች ሁለቱን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮች የማማከር ኃላፊነት ይኖርበታል።

### 2.7.4. የክልሎች የሽግግር አስተባባሪ ኮሚሽን

ይህ ኮሚሽን በሃያ አንድ አባላት የሚቋቋም ሲሆን የኮሚሽኑ ሰብሳቢም ከሁለቱ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮች አንዱ ይሆናል። የኮሚሽኑ ሰብሳቢም ሆነ አባላት የሚመረጡት በሦስቱ ጠቅላይ ሚኒስትሮች ድርድር ሲሆን፣ የኮሚሽኑ አባላት የሸንጎው አባላት የሆኑ ወይም ያልሆኑ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ከኮሚሽኑ ሃያ አንድ አባላት ውስጥም ዘጠኙ ክልሎችና ሁለቱ የፌደራል ከተሞች አንድ አንድ ተወካዮች ይኖሯቸዋል። የዚህ ኮሚሽን ዋና

ኀላፊነትም የሽግግር መንግሥቱ አስፈጻሚ አካል የሽግግሩን ሒደት በክልሎች ለማስፈጸም የሚያስችሉትን መዋቅሮች ማደራጀትና የሽግግር መንግሥቱን ኀላፊነቶች አፈጻጸም መከታተል ይሆናል።

### 2.7.5. የብሔራዊ ደኅንነት አስከባሪ ኮሚሽን

ይህ ኮሚሽን በሃያ አንድ አባላት የሚቋቋም ሲሆን የኮሚሽኑ ሰብሳቢ ከሁለቱ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮች አንዱ ይሆናል። የኮሚሽኑ አባላት የሚመረጡት በሦስቱ ጠቅላይ ሚኒስትሮች ድርድር ሲሆን የሚመረጡት አባላት የሸንጎው አባላት የሆኑ ወይም ያልሆኑ ሊሆኑ ይችላሉ። አብዛኞቹ ለዚህ ኮሚሽን የሚመረጡ ሰዎች በጸጥታና በውጭ ጉዳይ ሥራ በቂ ልምድና ዕውቀት ያላቸው መሆን ይገባቸዋል። የሀገሪቱ መከላከያ ኤታማዦር ሹም፣ የደኅንነት ቢሮ ኀላፊ፣ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽነርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የዚህ ኮሚቴ አባላት ይሆናሉ። ዘጠኙ ክልሎችና ሁለቱ የፌደራል ከተሞች በዚህ ኮሚሽን ውስጥ አንድ አንድ ተወካይ ይኖራቸዋል።

የዚህ ኮሚሽን ዋና ኀላፊነት የሽግግር መንግሥቱ በተቋቋመ በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ እስከ ቀበሌ አስተዳደር ድረስ ባለው የሀገሪቱ መዋቅር የራሱን “የሰላምና የሕግ የበላይነት አስከባሪ ኮሚቴ” አቋቁሞ በመላ ሀገሪቱ ሰላምንና የሕግ የበላይነትን ፈጣንና አስተማማኝ በሆነ መጠን ማረጋገጥ ይሆናል። በሽግግሩ ወቅት ማንኛውም በፌደራልም ሆነ በክልል ደረጃ ያለ የጸጥታ ተቋም (የክልል ልዩ ኀይልና ሚሊሻን ጨምሮ) በወጥነት የሚታዘዘው በዚህ ኮሚሽንና ይህ ኮሚሽን በተዋረድ በሚያቋቁማቸው የእዝ ኮማንዶች ብቻ ይሆናል። ኮሚሽኑ የሀገር ውስጥን ጸጥታ ከማስከበር በተጨማሪ ሀገሪቱን ከማንኛውም ዓይነት የውጭ ኀይሎች ጣልቃ ገብነትና ጥቃት የመጠበቅ ኀላፊነት ይኖረዋል። በተለይም ከግብጽ ሊመጣ የሚችልን ማንኛውም ዓይነት ጥቃት ለመከላከል የሚያስችል በቂ ዝግጅት የማድረግ ኀላፊነት ይኖረዋል።

### 2.7.6. የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሐሳብ አርቃቂ ኮሚሽን

ይህ ኮሚሽን በሃያ ሰባት አባላት የሚቋቋም ሲሆን የኮሚሽኑ ሰብሳቢ የፓርቲ አባል ያልሆነና በሕገ መንግሥት ጉዳዮች ላይ በቂ ዕውቀት ያለው ሰው ይሆናል። የኮሚሽኑ አባላት የሚመረጡት በሦስቱ ጠቅላይ ሚኒስትሮችና በግለሰቦች ስብስብ ጎራው ሰብሳቢ አማካኝነት በዐራትዮሽ ድርድር ሲሆን የሚመረጡት አባላት የሸንጎው አባላት የሆኑ ወይም ያልሆኑ ሊሆኑ ይችላሉ። አብዛኞቹ የዚህ ኮሚሽን አባላት የሕግና የፖለቲካ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ይሆናሉ። በዚህ ኮሚሽን ውስጥ ዐራቱ ተደራዳሪ ጎራዎች እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ተወካይ ይኖራቸዋል። ከኮሚሽኑ ሃያ ሰባት አባላት ውስጥም ዘጠኙ ክልሎችና ሁለቱ የፌደራል ከተሞች አንድ አንድ ተወካዮች ይኖሯቸዋል። የዚህ ኮሚሽን ዋና ኀላፊነት ከፖለቲካ ድርጅቶችና ከክልሎች ጋር በመወያየት፣ የተለያዩ የሕዝብ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት፣ የሕግ ዕውቀት ያላቸውን ምሁራን በማወያየት፣ የሌሎች ሀገራትን ልምድ በማጥናት አንድ የሕገ መንግሥት የማሻሻያ ረቂቅ ሐሳብ አዘጋጅቶ ለህዳሴ ሸንጎው ማቅረብ ይሆናል። ኮሚሽኑ በሚያካሂደው ጥናትም ማሻሻያ የሚደረግባቸውን ሕገ መንግሥታዊ አንቀጾች በሚከተሉት ሁለት ደረጃዎች ከፍሎ ለሸንጎው ያቀርባል።

**ማለትም፡-**

ደረጃ 1፡- አነስተኛና መለስተኛ ክብደት አላቸው ተብለው የሚታመንባቸው የሕገ መንግሥት የማሻሻያ አንቀጾች ከሽግግሩ ዘመን በኋላ በሕዝብ ተመርጦ በሚቋቋመው ፓርላማ የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት መሠረት እንዲሻሻሉ፤

ደረጃ 2፡- በደረጃ 1 ሊሻሻሉ የማይችሉና ዐራቱ ተደራዳሪ ጎራዎች መስማማት ያልቻሉባቸው የሕገ መንግሥት አንቀጾች በሕዝበ ውሳኔ /Referendum/ እንዲሻሻሉ የሚያስችል የውሳኔ ሐሳብ ለህዳሴ ሸንጎው ያቀርባል።

የሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽኑ በአጠቃላይ ሊሻሻሉ የሚገባቸውን አንቀጾች ከፍ ሲል በተጠቀሱት ሁለቱ ደረጃዎች ተለይተው እንዲቀርቡ የሚያደርገው፥ ዐራቱን ተደራዳሪ ጎራዎች አደራድሮ ከሚያገኘው ውጤት በመነሳት ይሆናል። በደረጃ አንድም ሆነ ሁለት የሚካተቱት ማሻሻያዎች መሻሻል እንደሚገባቸው ውሳኔ የሚያገኙት በሽግግር ጊዜው ሸንጎ ቢሆንም የሚሻሻሉት ግን በሽግግሩ ወቅት ሳይሆን በሕዝብ የሚመረጠው መንግሥት በተቋቋመ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ይሆናል። በሌላ አገላለጽ፥ የትኞቹ የሕገ መንግሥቱ አንቀጾች መሻሻል ይገባቸዋል? የሚለው ጥያቄ መልስ የሚያገኘው በሽግግሩ ወቅት ሲሆን፣ ይህንን ውሳኔና የቀረበውን የማሻሻያ ረቂቅ መሠረት ያደረገ ሕገ መንግሥታዊ ማሻሻያ የሚደረገው ግን የሕዝብ መንግሥት በተቋቋመ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ይሆናል ማለት ነው።

ኮሚሽኑ በሚያቀርባቸው ረቂቅ ሐሳቦች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን የሚኖረው የህዳሴ ሸንጎው ሲሆን፣ ሸንጎው ከላይ በተጠቀሱት በሁለት ደረጃዎች እንዲሻሻሉ የወሰናቸውን ሕገ መንግሥታዊ አንቀጾች ከነማሻሻያ ሐሳባቸው በሕዝብ ለሚመረጠው ፓርላማና ለምርጫ አስፈጻሚ ኮሚሽኑ ያስረክባል።

### 2.7.7. የእርቀ ሰላምና የሽግግር ጊዜ ፍትሕ አስፈጻሚ ኮሚሽን

ይህ ኮሚሽን በሃያ አምስት አባላት የሚቋቋም ሲሆን የኮሚሽኑ ሰብሳቢም ሆነ አባላቱ የሚመረጡት በሦስቱ ጠቅላይ ሚኒስትሮች ድርድር ይሆናል። የዚህ ኮሚሽን ሰብሳቢም ሆነ አባላት ሙሉ በሙሉ የፓርቲ አባል ያልሆኑ ሰዎች ይሆናሉ። በዚህ ኮሚሽን ውስጥ የሸንጎ አባል የሆኑም ሆነ ያልሆኑ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ የሕግ ምሁራንና ተጽእኖ ፈጣሪ ግለሰቦች፣ ታዋቂ ስፖርተኞችና አርቲስቶች በቂ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይደረጋል።

የዚህ ኮሚሽን ዋና ኀላፊነትም ባለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት ከሰብዓዊ መብትና ከኢኮኖሚ ጋር በተያያዘ የተፈጸሙ ወንጀሎች በምን አግባብ መፈታት እንዳለባቸው የተለያዩ የይቅርታና የፍትሕ አሰጣጥ አማራጮችን የሚያመላክት ረቂቅ ሀሳብ አዘጋጅቶ ለሸንጎው ማቅረብ፤ ባለፉት ሦስት በሀገራችን የተፈራረቁ መንግሥታት በሥልጣን ላይ የነበሩ ሰዎች በእነዚህ መንግሥታት ስለተፈጸሙ በደሎች መጸጸታቸውን በፈቃዳቸው የሚገልጹባቸውና በእነዚህ መንግሥታት በደል የደረሰባቸው ሰዎችም ስለደረሰባቸው በደል በይፋ ምስክርነታቸውን የሚገልጹባቸው መድረኮች በተለያዩ የሀገሪቱ ከተሞች ማዘጋጀት፤ አሁን በሥራ ላይ የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከአሁን በኋላ የሚያካሂዱት የፖለቲካ ትግል ሰላማዊና ሕጋዊ በሆነ መንገድ ብቻ እንደሚሆን ለሕዝቡ ቃል ኪዳን የሚገቡበት መድረኮች

ማዘጋጀት፣ እስካሁን በግጭት ውስጥ ላሉ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የኅብረተሰብ ክፍሎች የውይይትና ይቅር የመባባያ መድረኮችን መፍጠርና እነዚህን ተግባራት ሕዝቡን በሰፊው አሳታፊ በሆነ ሒደት በማከናወን በሀገሪቱ አዲስ የሰላም፣ የፍቅርና የመተባበር መንፈስ እንዲፈጠር ማስቻል ነው።

በመጨረሻም ይህ ኮሚሽን የሽግግር መንግሥቱን ታሪካዊ ስኬት በሚመለከት በብሔራዊ በዓልነት ሊከበር ስለሚገባው ቀንና በመታሰቢያነት ሊቆም ስለሚገባው የህዳሴ የእርቅና የአንድነት ሀገራዊ ኃውልት መነሻ ሐሳብ ለህዳሴ ሸንጎው ያቀርባል። ሸንጎው ኀላፊነቱን አጠናቅቆ በሕዝብ ለተመረጠው መንግሥት ሥልጣኑን በሚያስረክብበት ዕለት በሸንጎው ውሳኔ በተመረጠው ቦታ ላይ የኃውልቱ የመሠረት ድንጋይ እንዲተከል ያደርጋል። ትውልድ ይማርባቸው ዘንድም የኮሚሽኑን አጠቃላይ የሥራ ሒደትና በአጠቃላይም የሽግግር ሒደቱን አፈጻጸም የሚያሳዩ መረጃዎች በአግባቡ ተሰድረውና ተቀርጸው በልዩ ቤተ መዘክር ለእይታ እንዲቀርቡ ያደርጋል።

### 2.7.8. የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚሽን

ይህ ኮሚሽን በዘጠኝ አባላት የሚቋቋም ሲሆን የኮሚሽኑ ሰብሳቢም ሆነ አባላት የፓርቲ አባላት ያልሆኑና በገለልተኝነታቸው የሚታወቁ ሰዎች ይሆናሉ። እነዚህ የኮሚሽኑ አባላት የሚመረጡት በሦስቱ ጠቅላይ ሚኒስትሮችና በግለሰቦች ጎራው ሰብሳቢ የዐራትዮሽ ድርድር ሲሆን፣ የኮሚሽኑ አባላት የሸንጎ አባላት የሆኑም ሆነ ያልሆኑ ሰዎች ሊሆኑ ይችላል። የዚህ ኮሚሽን ዋና ኀላፊነትም በሽግግሩ ወቅት በሀገር ደረጃ በቂ ዝግጅት በማድረግ ምቹ ሁኔታ መፍጠርና በሀገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰላማዊ፣ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ ማካሄድ መቻል ይሆናል። በአጠቃላይ የሽግግር ጊዜ ዘመኑ የሚጠናቀቀው ይህ የምርጫ ኮሚሽን በሕዝብ የተመረጠው መንግሥት ሥልጣኑን ከሽግግር መንግሥቱ እንዲረከብ በሚያደርጉበት ዕለት ይሆናል። ነገር ግን በሕዝብ የሚመረጠው መንግሥት ካመነበት የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚሽኑን ቋሚ የሀገሪቱ የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚሽን ሆኖ እንዲቀጥል ሊያደርግ ይችላል።

## 2.8. የክልሎች የሽግግር ሥራ አስፈጻሚ ካውንስል

የክልል የሽግግር ሥራ አስፈጻሚ ካውንስሎች በዘጠኙ ክልሎችና በሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች ይቋቋማሉ። የካውንስሎቹ አባላት ቁጥር 30 ሲሆን፣ እነዚህ አባላት ዐሥሩ ከክልሉ ገዥ ፓርቲ፣ ዐሥሩ በክልሉ ከሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ ዐሥሩ ደግሞ የፖለቲካ ፓርቲ አባል ካልሆኑ የተለያዩ የክልሉ ኗሪ ከሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከሚወከሉ ግለሰቦች የተውጣጣ ይሆናል። ከተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚወከሉትን ዐሥር ሰዎች በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተመካክረውና ተደራድረው መምረጥ የሚጠበቅባቸው ሲሆን፣ ከግለሰቦች የሚመረጡትን ዐሥር ሰዎች ደግሞ የክልሉ ገዥ ፓርቲና ተቃዋሚ ፓርቲዎቹ ተመካክረው መምረጥ ይጠበቅባቸዋል። የካውንስሉ ሰብሳቢ ከክልሉ ገዢ ፓርቲ የሚመረጥ ሲሆን፣ ከተቃዋሚ ፓርቲዎችና ከግለሰቦች ስብስብ የሚመረጡ ሁለት ምክትል ሰብሳቢዎች ይኖሩታል። በክልል የሚገኙት ፓርቲዎች አደረጃጀት በፌደራል ደረጃ የሚኖረውን የአደረጃጀት ሥልት የተከተለ ይሆናል።

የካውንስሉ ዋና ኀላፊነቶች የክልሎቹንና የከተማ አስተዳደሮቹን የዕለት ተዕለት ሥራ መምራትና ከሽግግር መንግሥቱ የሚሰጡትን ተጨማሪ ኀላፊነቶች በክልል ደረጃ ማስፈጸም ይሆናል። የክልሎች የሽግግር ሥራ አስፈጻሚ ካውንስሎች የሚያስፈጽሟቸው ዝርዝር ኀላፊነቶችና የውስጥ የአሠራር ደንቦች ተቀርጸው የሚሰጧቸው ከሽግግር መንግሥቱ የክልሎች የሽግግር አስተባባሪ ኮሚሽን ይሆናል። የክልሎች የሽግግር ሥራ አስፈጻሚ ካውንስሎች ለሽግግር መንግሥቱ የሥራ አስፈጻሚ ካውንስልና ለክልሎች የሽግግር አስተባባሪ ኮሚሽኑ ጣምራ ተጠሪነት ይኖራቸዋል። በሽግግር መንግሥቱ የተለያዩ መዋቅሮች ውስጥ ክልሎችንና የከተማ መስተዳድሮችን የሚወክሉ አባላትን የመምረጥና የመወከል መብት የሚኖረውም ይህ የክልል የሽግግር ሥራ አስፈጻሚ ካውንስል ይሆናል። ካውንስሉ ክልሉን የሚያስተዳድር ምክር ቤት በሕዝብ ተመርጦ ሥልጣኑን እስከሚረከበው ድረስ የሚኖረው ሥልጣን ሕግ የማስፈጸም እንጂ ሕግ የማውጣት አይሆንም።

መጋቢት፥ 2012 ዓ.ም.

ልደቱ አያሌው

<u>ማሳሰቢያ</u>፡-

በዚህ ለውይይት በቀረበ የመነሻ ሐሳብ ላይ አስተያየት መስጠት የምትፈልጉ ዜጎች፥ ጽሑፉ ይፋ በሆነ በ20 ቀናት ውስጥ (እስከ መጋቢት 20፥ 2012 ዓ.ም.) አስተያየታችሁን በሚከተለው የኢሜል አድራሻ መላክ ትችላላችሁ።

ethiopiacomment@gmail.com